Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ


**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**


**የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር**

# በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ መንግስታዊ በሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውሰጥ አተገባበር (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)


**በ አሸናፊ ሞገስ**



መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ መንግስታዊ በሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

አሸናፊ ሞገስ

አማካሪ

ታደሰ ሲባሞ ዶ/ር



መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

**በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ መንግስታዊ በሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)**

ለተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

**በ**

**አሸናፊ ሞገስ**

የፈተና ቦርድ አባላት

____________________________ __________

አማካሪ ፊርማ

____________________________ __________

ፈታኝ ፊርማ

____________________________ __________

ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና

በመጀመሪያ ሙሉ ጤናዬን ሰጥቶ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ሰርቼ እንድጨርስ ለረዳኝ ለድንግል ማሪያም ልጅ ቸሩ ልዑል እግዚአብሄር ስሙ ለዘላለም በፍጥረት አንደበት የተመሰገነ እና የተወደሰ ይሁን፡፡ እንዲሁም የማስተርስ ትምህርት እድል በነጻ ሰጥቶ ላስተማረኝ እና በክብር ላስመረቀኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለው፡፡

በመቀጠል ያለባቸውን የስራ ጫና ተቋቁመው የጥናቴን ርዕስ ከማጽደቅ አንስቶ ረቂቁን በማንበብና አስፈላጊውን እርማትና ማስተካከያ በመስጠት እንዲሁም ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ለተባበሩኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ታደሰ ሲባሞ ልባዊ ምስጋናዬን ረጅም እድሜ ከጤና ጋር አብዝቶ ፈጣሪዬ እንዲሰጥልኝ እመኛለሁ፡፡

ለጥናቴ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በቅንነት በመስጠትና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማሟላት ለተባበራችሁኝ መምህራንና የአስተዳደር አካላት ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ጥናቴን ጀምሬ እስከምጨርስ ከጎኔ ላልተለዩኝ ውድ ቤተሰቦቼ እና የቅርብ ጓደኞቼ ላደረጋችሁልኝ ድጋፍና ትብብር በልዑል እግዚአብሄር ስም ያለኝን አክብሮት ከልቤ መግለጽ እወዳለሁ፡፡

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና ...................................................................................................................... I
የሰንጠረዥ ማውጫ ...................................................................................................... IV
አጠቃሎ ..................................................................................................................... V
ምእራፍ አንድ ............................................................................................................ 1
መግቢያ ...................................................................................................................... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ............................................................................................................ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት .......................................................................................... 4
1.3 የጥናቱ ዓላማ .......................................................................................................... 6
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ...................................................................................................... 6
1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................................................................................... 7
1.6 የጥናቱ ውስንነት ...................................................................................................... 7
1.7 የቁልፍ ቃላት እና ጽንሰሃሳቦች ብያኔ ........................................................................... 7
ምዕራፍ ሁለት ............................................................................................................. 9
የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ .............................................................................................. 9
2.1 የአንብቦ መረዳት ምንነት ........................................................................................... 9
2.2 የማንበብ ብልሃት ምንነት .......................................................................................... 13
2.3 የማንበብ ብልሃት ጠቀሜታ ........................................................................................ 14
2.4 የማንበብ ብልሃት አይነቶች ........................................................................................ 15
2.5 በብልሃቶች አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ............................................... 17
2.6 ማንበብን ማስተማሪያ ዘዴ ......................................................................................... 18
2.6.1 የተለመደው የማንበብ የማስተማሪያ ዘዴ ..................................................................... 18
2.6.2 ሚና ለዋጭ ዘዴ (Reciprotical Teaching) ................................................................ 19
ምዕራፍ ሶስት .............................................................................................................. 21
የአጠናን ዘዴ .............................................................................................................. 21
3.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች ................................................................................................. 21
3.2 የናሙና አመራረጥ .................................................................................................... 21
3.2.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ................................................................................. 21
3.2.2 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ .................................................................................. 22
3.2.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........................................................................................ 22
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ................................................................................. 22

3.3.1 ምልከታ ........................................................................................................ 22
3.3.2 የጽሁፍ መጠይቅ ................................................................................................ 23
3.4 የአጠናን ሂደት ...................................................................................................... 23
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ .............................................................................................. 23
ምዕራፍ አራት ............................................................................................................ 24
የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ .......................................................................................... 24
4.1 የውጤት ትንተና ..................................................................................................... 24
4.1.1 በ2ቱ ትምህረትቤቶች የተካተቱ መምህራን ምልከታ የተገኘው ውጤት ትንተና..... 25
4.2 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግንዛቤ .................................... 38
4.2.1 የቅድመ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግንዛቤ .................................. 39
4.2.2 የንባብ ጊዜ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግንዛቤ ....................................... 40
4.2.3 የድህረ ንባብ ብልሃቶች አተገባበር ግንዛቤ ........................................................... 43
4.3 በአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች 45
4.4 ጥናቱ የውጤት ማብራሪያ ....................................................................................... 47
ምዕራፍ አምስት .......................................................................................................... 51
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች .......................................................................................... 51
5.1 ማጠቃለያ ........................................................................................................... 51
5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች .................................................................................................. 52
ዋቢ ፅሁፎች ............................................................................................................... 54
አባሪዎች .................................................................................................................... 59
አባሪ ሀ. የምልከታ መገምገሚያ ቅጽ .................................................................................. 59
አባሪ ለ. የጽሁፍ መጠይቅ ቅጽ ....................................................................................... 62

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 4.1.1.1 የቅድመ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን አንጻር ሲተነተን ........ 25
ሠንጠረዥ 4.1.1.2 የንባብ ጊዜ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን አንጻር ሲተነተን ........ 30
ሠንጠረዥ 4.1.1.3 የድህረ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን አንጻር ሲተነተን ........ 34

# አጠቃሎ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር መመልከት ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ተሳታፊ እንዲሆኑ የተመረጡት በጉመር ወረዳ በጀንቦሮ እና አረቅጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች በ2015ዓ.ም 9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን ሁሉም ናቸው፡፡ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች  የጽሁፍ መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡ የመምህራኑን የቅድመ ንባብ ፣ንባብ ጊዜና የድህረንባብ ብልሃቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበርና ግንዛቤ ለመፈተሽ የሚያስችል ቅጽ ምልከታው ከተከናወነ በኋላ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ  የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች በመጠናዊና በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት በሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ በአጠቃላይ የምልከታው ውጤት ምን እንደሆነ አመልክቷል፡፡ በተመሳሳይ መምህራኑ ስለቅድመ ንባብና የንባብ ጊዜ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሆነ አሳይቷል፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት ጥናቱ የሚመለከታቸው መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ እንዲሁም በመምህራኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ተግዳሮቶችን ለይቷል፡፡ በመጨረሻም ከጥናቱ ውጤትና ድምዳሜ በመነሳት የመፍትሄ ሃሳቦችና አስተያየቶች ተሰጠተዋል፡፡

# ምእራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ማንበብ አንድን በጽሁፍ የሰፈረን ምንባብ መልእክት በጥልቀት ማለትም ጸሃፊው በጽሁፍ ቃል በቃል ማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት በጥልቀት መርምሮ መረዳት ነው። ይህንንም በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየግላቸውን ሀሳብ ስንዝረዋል። ሀሳብ ከሰነዘሩት ውስጥ William (1984፡3) ‹‹ማንበብ ተፈላጊውን መረጃ የማግኘትና የመረዳት ሂደት ነው። የመረዳቱ ሁኔታም ከሚያነቡበት አላማ የማንበቢያ ስልት የተለያየ ሊሆን ይችላል” ብለዋል። እንዲሁም Grellt (1981፡3) የአነባብ ስልትን መለያየት “ከማስታውቂያ ፍሬ ሀሳቡን በገረፍታ የሚነበብ ሲሆን ሳይንሳዊ ምርምርን ግን በጥልቀት ማንበብን ይጠይቃል” በማለት ገልጸዋል።

ከነዚህ ምሁራን የምንረዳው ሃሳብ አንድን ጽሁፍ ስናነብ የምናነብበት አላማና የአነባበባችን ስልት እንደሚለያይ ነው።ማንበብ ከመቀበል ክሂል አንዱ ሲሆን ከጽሁፍ ውስጥ ፍሬ ሀሳብን ለይቶ ማውጣት ፣የጽሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳት፣ የቃላት አውዳዊ ፍቺዎች መገንዘብ እና የጸሃፊውን ሃሳብ መረዳት እንደሆነ Harmer (2001) ያስገነዝባሉ። እንዲሁም Davies (1995) ንባብ በግል የሚከናወን ተግባር ከመሆኑም ባሻገር በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ የሚገኝን ጸሀፊ መልዕክት በመረዳት ምላሽ ለመስጠት የምንሞክርበት አእምሮአዊ ተግባር እንደሆነ ይገልጻሉ።

ከነዚህ ምሁራን መረዳት የሚቻለው ከምናነበው ጽሁፍ ውስጥ ጠቃሚ መረጃ ናቸው የምንላቸውን ይዘቶች(መሰረታዊ ሃሳቦች) ለይቶ ማውጣት እና መረዳት የሚቻለው በማንበብ እንደሆነና በግል የሚከናወን ተግባር ከመሆኑም ባለፈ የደራሲውን ጽሁፍ ሃሳብ ተረድተን ግብረ መልስ ለመስጠት የምንሞክርበት ተግባር እንደሆነ ነው።

እንደ Snow (2002) ገለጻ አንብቦ መረዳት ቅድመ ንባብ ፣የማንበብ ጊዜ እና ድህረ ንባብ ክንውኖችን ያስተናግዳል። እነዚህ አነስተኛ የማንበብ ጊዚያት ለአንብቦ መረዳት ወሳኝ ቅደምተከተላዊ ክንውኖች ናቸው። ምክንያቱም አንባቢው በማንበብ ወቅት ያመጣውን ወይም የተጠቀመበትን የቀደመ እውቀት እና በአንባቢው ጽሁፍ ውስጥ ባገኘው አዲስ እውቀት መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት ይጠቅማል። እያንዳንዱ የማንበብ ክንውን የራሱ የሆነ አነስተኛ የእድገት ሂደት አለው።በሂደቱ አንባቢው አእምሯዊ (ግንዛቤያዊ) ብቃቱ ሲጎለብት እና

ተጨማሪ ልምድ ሲያገኝ እንዲሁም የበለጠ አስቸጋሪ ውህድ አሃድ ሲገጥመው እና ሲታገል ከትምህርቱ ይጠቀማል።

የአንብቦ መረዳት ትምህርት አንባቢዎች የቀደመ እውቀታቸውን አዲስ ከሚያነቡት ጽሁፍ ጋር መስተጋብር ፈጥረው መልእክቱን የሚረዱበትና የሚተረጉሙበት ሂደት ነው።አንብቦ መረዳት በሂደትና በብልሃቶች የሚነበብ ክሂል ነው።የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አንብቦ መረዳትን ለማጎለበት የሚያስችሉ ናቸው።አንብቦ መረዳትን የሚያጎለብቱ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ቢኖሩም ቁልፉን ድርሻ የሚይዘው የአንባቢውን የቀደመ እውቀት በመቀስቀስ አዲስ ከሚቀርበው እውቀት ጋር ማገናኘት ነው።

እንደ Rowell እና Palmer (2007) አገላለጽ አንብቦ መረዳት በጽሁፍ ከቀረበ ሀሳብ ጋር መስተጋብር በመፍጠር ፍቺን ፈልፍሎ ማውጣት እና መልሶ የማዋቀር ሂደትን የሚያስተናግድ ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት ነው።ይህም ሁሉንም የማንበብ ሂደት መሰረታዊ ነገሮች (ፊደልን እና ቃላትን መለየት፣ ቅላጼ ፣የሃሳብ ፍሰትን ጠብቆ ማንበብ እና አንብቦ መረዳት) በጋራ በማሳተፍ አንብበው የውህድ አሀዱን አጠቃላይ ምስል (ይዘት እና ቅርጽ) እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው ይላሉ።

ከላይ ከተገለጸው ሃሳብ መረዳት የምንችለው የአንድን ጽሁፍ መልእክት አንብቦ ለመረዳት ከጽሁፉ መልእክት(ሀሳብ) ጋር መስተጋብር መፍጠር ብቻ ሳይሆን በምናነብበት ጊዜ ፊደላትን እና ቃላትን መለየት፣ የሃሳብ ፍሰትን ጠብቆ ማንበብና ይዘቱን መረዳት እንዲሁም በአጠቃላይ መልእክቱን መረዳት እንዳለብን ነው።

አንብቦ መረዳት ተማሪዎችን የቋንቋ እና የቃላት እውቀት ከፍ በማድረግ ለአዲስ መረዳት እና ለአርቆ ማስተዋል ያዘጋጃቸዋል።ውጤታማ (ጠንካራ)አንባቢዎች የተለያዩ ውህድአሃዶችን አንብበው ለመረዳት በተደጋጋሚ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅተው ይጠቀማሉ(Pressley 2002፡22)።

ማንኛውም ሰው ቢሆን የቀደመ እውቀት አለው።በክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ስለሚያነቡት ጽሁፍ የቀደመ እውቀት አላቸው።ስለሆነም ያንን የቀደመ እውቀት በመቀስቀስና በመገንባት አዲስ ከሚያገኙት እውቀት ጋር እንዲያስተሳስሩት የሚያስችሏቸውን ብልሃቶች መሰረት አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ የመምህራን ድርሻ ይሆናል (Ajidhe 2006)።

Alfassi (2004) እና Wei (2005) አንድን ጽሁፍ ለማንበብ የማንበብ ችሎታ መዳበር ወሳኝ ሲሆን በመማር ማስተማር ሂደት በየትኛውም ትምህርት ሁኔታ አንድን ነገር ለመረዳትም ሆነ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አንብቦ መረዳት መቻል አስፈላጊ ነው፡፡

እንደ Aloqaili (2012) አገላለጽ የአንብቦ መረዳት ጉዳይ በዳራዊ እውቀትና አሁን በሚነበበው ጽሁፍ መካከል አንባቢው የሚያደርገው መስተጋብራዊ ሂደት ነው፡፡ አንባቢዎች እንዳላቸው ዳራዊ እውቀት ልዩነት አንድን ጽሁፍ በተለያየ ደረጃ ሊረዱት ይችላሉ፡፡ ስለሚነበበው ጽሁፍ የተሻለ ዳራዊ እውቀት ያላቸው ተማሪዎች ቁንጽል ዳራዊ እውቀት ካላቸው ተማሪዎች በተሻለ መልኩ አንብበው ይረዳሉ፡፡ይህንኑ ሃሳብ Conley (1992) ሲያጠናክሩት ስለሚነበበው ጽሁፍ ተጨማሪ ዳራዊ እውቀት ያላቸው አንባቢዎች በሚያነቡበት ጊዜ ትኩረት የሚያደርጉት ሰፊና ጠቃሚ ጽንሰሃሳቦች ላይ ነው፡፡ ይህም የጽሁፉን ጭብጥ በፍጥነት እንዲረዱና ጠቃሚ የሆኑ ዝርዝር ጉዳዮችንም እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል ይላሉ፡፡

አንብቦ መረዳት በተከታታይ በሚደረግ ልምምድ ደረጃ በደረጃ እየዳበረ የሚሄድ ክሂል ነው፡፡ Davis (2011) እና Tankersiey (2005) እንደሚያስረዱት አንብቦ መረዳት በሂደት የሚገነባ ክሂል ነው፤ በተወሰነ ጊዜ የሚዳብረ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ በሚደረግ ልምምድ ሳቢያ በአዕምሮ ውስጥ የሚከናወን እድገትም ነው፡፡ ተማሪዎች ደጋግመው ሲያነቡ በህይወት ዘመናቸው የቀደመ እውቀታቸውንና አረዳዳቸውን  እያሳደጉ ይቀጥላሉ፡፡

Gray (2008) እንዳብራሩት በእውቀት ግንባታ በዋናነት መከናወን ያለበት አዳዲስ ሃሳቦችን በቀጥታ መቀበል ሳይሆን ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን አዲስ ከሚያነቡት ጽሁፍ ጋር በማዋሃድ መስተጋብር እንዲፈጥሩ ማድረግ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው በእውቀት ግንባታ ንድፈ ሃሳብ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ተማሪዎች በንቃት ተሳታፊ ሆነው የቀደመ እውቀታቸውን መነሻ በማድረግ አዲስ እውቀት የሚገነቡበት ክሂል መሆኑን ነው፡፡ በተመሳሳይ Anderson (1999) እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ትምህርት ተማሪዎች ተቀባይ ወይም ተመልካች የሚሆኑበት ሂደት አይደለም፡፡ ይልቁንም የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም ከሚነበበው ጽሁፍ እውቀት ለማግኘት ንቁ ተሳትፎ የሚደረግበት ነው፡፡

በሌላመልኩ Davis (2011) እንደገለጹት ስለአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲታሰብ ከመምህራን የሚጠበቀው ተግባር ተማሪዎች ንቁ አንባቢ እንዲሆኑ በመስተማር ዘዴያቸው ውስጥ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዴትና መቼ እንደሚጠቀሙባቸው እያሰላሰሉና እየተገበሩ በማሳየት

ከዚያም ከተማሪዎች ጋር አብረው እያለማመዱ በሂደት ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲተገብሩ ማስቻል ነው፡፡ ምክኒያቱም ንቁ አንባቢዎች የቀደመ እውቀታቸውን መሰረት በማድረግ ጽሁፉን ከማንበባቸው በፊትም ሆነ እያነበቡ ቀጥሎ ስለሚመጣው ጉዳይ ይገምታሉ፤ የሚያነቡትን ጽሁፍ ይዘት ይገነዘባሉ፤ የተገነዘቡትን ይዘት ይመረመረምራሉ፤ ይገመግማሉ፡፡

በአጠቃላይ Aloqaili (2012) በክፍል ዉስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ይለያያል፡፡ ለችሎታቸው መለያየት ምክኒያቱ የአዕምሯዊ ብቃት መለየት ብቻ ሳይሆን የብልሃቶችን አጠቃቀም ካለመረዳት የሚመጣ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በተለያየ ሁኔታ የሚቀርብላቸውን ጽሁፍ አንብበው የመረዳት ችሎታቸው እንዲዳብር የብልሃቶችን አጠቃቀም የመምራትና የማገዝ ሃላፊነት የሚጣለው በመምህራን ላይ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

Hoftman፣Boamann እና Afflerbach(2000) የተባሉ ተመራማሪዎች እንደሚገልጹት እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ከ1963 ወዲህ በማንበብ ብልሃት ላይ ከ25,000 በላይ ጥናቶች እና ህትመቶች ተከናውነዋል፡፡ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ጥናቶችና ህትመቶች ተደራሽ የሆኑት "ጆርናሎች" ላይ የታተሙ ባለመሆናቸው ብዙ የቋንቋ መምህራን አያውቋቸውም፡፡በመሆኑም በመምህራን የማንበብ ትምህርት አመለካከትና አተገባበር ለይ ያመጡት ለውጥ በጣም አነስተኛ ነው ይላሉ፡፡ አክለውም ማንበብ አዕምሯዊ ብልሃቶችን(cognitive strategies) ለተማሪዎች ማስተማር ተማሪዎቹ ብልህ አንባቢዎች እንዲሆኑና አንድን ጽሁፍ አንብበው በመረዳት ሂደት ውጤታማ እንዲሆኑ በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይገልጻሉ፡፡ Davies (1995) እንደሚገልጹት ደግሞ ብልሃት(strategy) አንብቦ መረዳትን ወይም መማርን አላማው ያደረገ ሆን ተብሎ ወይም ሳይታሰብ ጥቅም ላይ የሚውል አዕምሯዊ ወይም አካላዊ ተግባር ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው የማንበብ ብልሃቶች አንድ አንባቢ ከአንድ ጽሁፍ የሚገኙ መረጃዎችን በአእምሮው ለመመዝገብና ወደ ኂላ ለይ ለማስታወስ ይረዱት ዘንድ የሚጠቀምባቸው ድርጊቶች መሆናቸውን ነው፡፡ እንደWallace (1992) አገላለጽም የብልሃቶች አጠቃቀም እንደውህድአሀዱ ባህርይ፣ እንደአንባቢው አላማና እንደማንበቡ አውድ ሊለያይ ስለሚችል ብልሃቶችን በማስተማር ሂደት ይህን ሁኔታ ከግምት ማስገባት ያስፍልጋል፡፡

ተማሪዎች በማንበብ ትምህርት ወቅት የአንብቦ መረዳት አእምሯዊ ብልሃቶችን መማራቸው በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ከነዚህም መካከል አንብቦ መረዳትን ችግር መቅረፍ፣የማስታወስን

ችሎታ መጨመርና ሂሳዊ አስተሳሰብን ማዳበር ይጠቀሳሉ(Palincsar እና Brown፣1984)። ማሪው (1998) እንደሚገልጹት እንደገና መናገር ፣መገመት፣ዋናውን ሃሳብ ማውጣት፣ ማጠቃለልና ምስል መፍጠር የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር፣ክሂልን በማጎልበት ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው ይላሉ።

Moates (1999) እንደገለጹት በመማር ማስተማር ሂደት ማንበብ አስፈላጊ መረጃን ለማግኘት የሚያስችል መሰረታዊ ክሂል ነው።የማንበብን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አሉ።ይሁንና አንብቦ መረዳትን ከፍ ለማደረግ ከሚነበበው ጽሁፍ አላማ ጋር አብረው የሚሄዱ ብልሃቶች መጠቀምን ይጠይቃል ይላሉ።

የአንብቦ መረዳት ግብ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው አንብበው እንዲረዱ ማስቻል ነው። ተማሪዎች ሜታኮግኒቲቭ ብሃቶችን ተጠቅመው አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ እንዲያሰላስሉ፣እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው እራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ፣የአረዳዳቸውን ሁኔታ እንዲከታተሉና እንዲገመግሙ ብቁ ያደርጋቸዋል(Davis፣2011)።ይህንን ሃሳብ Tankersiey (2005) ሲያጠናክሩት ትክክለኛ መረዳት የሚገኘው አንባቢው የሚያዳምጠውንና የሚያነበውን ጽሁፍ በሜታኮግኒቲቭ ደረጃ መስተጋብር መፍጠር ሲቻል ነው ይላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ አጥኚው ካለው የግል ተሞክሮ እና ልምድ በጉራጌ ዞን አስራ አንድ ዓመት በላይ በመምህርነት ሙያ ሲሰራ ከተገነዘባቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃት አተገባበር ላይ ክፍተቶች መኖር ለዚህ ጥናት መደረግ አንዱ ግፊት የፈጠረ ጉዳይ ነው።

ሌላው ከተለያዩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስምንተኛ ክፍልን ጨርሰው አጥኚው ወደሚሰራበት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚመጡ አዳዲስ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት መቀነሱ ሌላው አነሳሽ ምክኒያት ሲሆን ለዚህም ችግር የመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ቢፈተሽ የሚል ግፊት በአጥኙው ላይ ማደሩ ሌላው አነሳሽ ምክኒያት ነው፡ እንዱሁም በዚህ ርእስጉዳይ ዙሪያ በውጭ አለም የተሰሩ ትናቶች ርእስ በመማር ማስተማር ዙሪያ አስፈላጊ መሆኑን መግለጻቸውና በኛ አገርም እንብዛም ያልተሰራበት መሆኑ አጥኚው በጉመር ወረዳ በሞገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መካከል በተመረጡ ትምህርትቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃት የክፍል ውስጥ አተገባበርን ለመፈተሽ ተነሳስቷል።

በዚህም መሰረት ጥናቱ ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል፡፡

1. በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ምን ያህል ተግባራዊ እያደረጉ ነው?
2. በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?
3. በሁለቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳይተገብሩ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጉመር ወረዳ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውሰጥ አተገባበር መፈተሽ ሲሆን ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡

1. በጉመር ወረዳ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ያላቸውን ግንዛቤ መፈተሽ
2. በጉመር ወረዳ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ አተገባበራቸውን መቃኘት
3. በጉመር ወረዳ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በክፍል ውስጥ ተግዳሮቶችን መለየት

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ግንዛቤ ኖሯቸው እንዲተገብሩትና ሙያቸውን እንዲያሻሽሉ ያግዛል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን

የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በክፍል ወስጥ የማይተገብሩ ከሆነ ባለመትግበራቸው ምክንያት የሚፈጠር የአንብቦ መረዳት ክፍተት እንዳለ እንዲያቁ ያግዛል፡፡

2. መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በክፍል ውስጥ እንዳይተገብሩ ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉትን ሁኔታዎች መለየት የሚያስችላቸውን ግንዛቤ እንዲፈጥሩ እድል ይሰጣል፡፡
3. ወደፊት በአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ዙሪያ ምርምር ማድረግ ለሚሹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መረጃ ይሰጣል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መካከል በተመረጡ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያንብቦ መረዳት ብልሃት አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ላይ ያተኩራል፡፡ በወረዳው ያሉ ሁሉንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችን ማካተት ቢቻል የተሻለ እንደሚሆን አጥኙው ያምናል፡፡ ነገር ግን ከጊዜና ከበጀት እጥረት አንጻር መጣም አድካሚ በመሆኑ ሌሎች ቀሪ ትምህርትቤቶች አያካትትም፡፡

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ የሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መካከል በሁለቱ ውስጥ የሚሰሩ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ያተኩራል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

በጥናቱ ርእሰጉዳይ ዙሪያ ብዙም የተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎች አለመኖር ጥናቱን ለማነጻጸር አስቸጋሪ መሆኑና ጥናቱ በጉመር ወረዳ በሚገኙ ሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አለማካተቱ የዚህ ጥናት ውስንነት ነው፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላት እና ጽንሰሃሳቦች ብያኔ

**አንብቦ መረዳት**፡-ተማሪዎች ለማንበብ ተግባር ከቀረበላቸው ጽሁፍ ጋር መስተጋብር በመፍጠር የጽሁፉን ፍቺ መለየት እና በአእምሯቸው ውስጥ መልሰው በማዋቀር እንዲሁም ከቀደመ

እውቀታቸው ጋር በማገናኘት ትርጉም ያለው ሀሳብ የሚያዋቅርበት ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት ነው፡፡

**የማንበብ ብልሃት**፦ተማሪዎች ለማንበብ የተሰጠን ውህድ አሃድ አንብበው ለመረዳት በንቃተህሊና ሆንብለው የተጠቀሙበት ዘዴ፣እቅድ፣የአእምሯሮ ተልኳዊ አሰራር ወይም ቅደም ተከተል ነው፡፡የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ጽሁፍ አንብበው ለመረዳት ብቻ ሳይሆን የጽሁፉ ሃሳብ ባልገባቸው ጊዜ (ችግር በገጠማቸው ጊዜ) ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመገንዘብ እርምጃ የሚወስዱበት መንገድ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

## 2.1 የአንብቦ መረዳት ምንነት

ሰርካለም ( 2010) Chair (2002) እና Williames (1990)ን ጠቅሰው እንደሚገልጹት አንብቦ መረዳት ማለት በአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚተላለፈውን መልእክት መገንዘብ እና ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ ማውጣት መቻል ሲሆን ጥልቅ ግንዛቤን የሚጠይቅ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡እንዲሁም Snow & Sweet (2003)እና Chair (2002) አንብቦ መረዳት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የምንፈልገውን ነገር መርጠን በማውጣት ትርጉም መስጠት ወይም መረዳት እነደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ሀሳብ አገላለጽ በጽሁፉ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አንቀጾች ያላቸውን የእርስበርስ ቁርኝት መረዳት ተገቢ ነው፡፡

Sheng (2000) እና Grellet (1990) እንደሚገልጹት አንብቦ መረዳት በአንባቢውና በጸሃፊው መካከል የሚደረግ መስተጋብር ሲሆን በሁለት መንገድ ከፍሎ ማይት ይቻላል፡፡ አንደኛው በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ ጉዳዮችን መገንዘብ፣ በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ የቀረቡትን ዋና ዋና ሀሳቦች መረዳት፣ በግልጽ የሚታዩ ሁኔታዎችን፣ ክስተቶችን፣ ድርጊቶችን ወዘተ ቅደምተከተል ማስታወስ፣ ግልጽ የሆኑ አንድነቶች እና ልዩነቶችን መለየት ወዘተ. ሲያካትት ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎቹ ተጠየቃዊ እውቀትን እና ግምትን በመጠቀም በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

Williames (1984፡15) አንብቦ መረዳት የምንለው አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙ ፍንጭ አመላካቾችን በመጠቀም መልእክቱን የሚቀበልበትን እና ግንዛቤውን የሚያዳብርበት ሂደት ነው፡፡ ይህም አዲሱን ጽሁፍ መልእክት ቀደም ሲል አዕምሮ ውስጥ ከነበረው ሃሳብ ጋር በማዛመድ እየገመገመ የሚቀበልበት ወይም አዲስ አዕምሯዊ ምስል የሚከሰትበት ነው፡፡ በሂደቱም ቀደም ሲል በነበረው ግንዛቤ መሰረት ከጽሁፉ አገኛለው ብሎ የገመተው ነገር ትክክል ስለመሆን አለመሆኑ እያረጋገጠ ወይም እያስተካከለ ግንዛቤውን ያሰፋል፡፡ ይህን ማድረግም የቃላትን ፍቺ፣ ሰዋሰዋዊ አያያዦችን፣ የሃሳብ አደረጃጀቶችን መገንዘብ እና በጽሁፉ ውስጥ

በግልጽ የቀረቡ ወይም ያልቀረቡ ነጥቦችን መለየት እና የተገኘውን መልእክት ከቀደመ እውቀት ጋር እያቀናጁ የመገንዘብ ችሎታ የሚጠይቅ ነውና ሊያዳብረው ይገባል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሰርካለም (2010) አንብቦ መረዳት ከጽሁፍ ውስጥ ጠቃሚ እና አዳዲስ መረጃዎችን ለይቶ ማውጣት እና የጽሁፉን መልእክት መረዳት ብቻ ሳይሆን በምንባቡ ውስጥ ከሰፈሩት የተለያዩ መረጃዎች በመነሳት የራስን ግንዛቤ ማስፋት፣ የጽሁፉን አደረጃጀት መለየት፣ አረፍተነገሮች ያላቸውን አገልግሎት መረዳት እና ተገቢ የሆኑ የማንበብ ብልሃቶች መጠቀምን ያካትታል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

በረከት (2010፡8) እንደሚያብራሩት አንብቦ መረዳት ተግባርን በሁለት መልኩ ከፍለው ያብራራሉ፡፡ የመጀመሪያው በሚቀርበው ምንባብ ውስጥ በግልጽ የቀረቡ መልእክቶችን ያለምንም ልፋት አንብቦ መረዳትን የሚያመለክት ሲሆን በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና መልእክቶች መገንዘብን፣ በግልጽ የተቀመጡ ሁነቶችን ፣ ድርጊቶችን፣ ክስተቶችን ወዘተ. ቅደም ተከተል ማስታወስን፣ በጽሁፍ ውስጥ ያለምንም ማሻሚት በግልጽ የሰፈሩ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን መለየት መቻልን፣ የምክንያት እና ውጤት ትስስርን ማስታወስን ወዘተ. የሚገልጽ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ያለው የአንብቦ መረዳት ተግባር ደግሞ ተማሪዎች ተጠየቃዊ እውቀትንና ግምትን በመጠቀም በጽሁፍ ውስጥ ግልጽ በሆነ መልኩ ያልተቀመጡ ሃሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ የሚጠቁም ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ አንብቦ መረዳት ችሎታ ደግሞ በግልጽ ከሚታዩት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ መለየትን፣ ፍሬ ሃሳብን ወይም ጭብጡን መለየትን፣ ደጋፊ ሀሳቦችን ለይቶ ማወቅን፣ በምክኒያትና ውጤት ትስስር የተነሳ ተከትሎ ሊመጣ ይችላል ተብሎ የሚገመትን ነገር መገመትን፣ በጽሁፍ ውስጥ ግልጽ በሆነ መልኩ የተቀመተውን መነሻ ሀሳብ በፍንጭነት በመጠቀም የገጸባህሪያትን ባህሪ መገንዘብን፣ ጸሃፊው የተጠቀመበትን ቋንቋ ፍች በትክክል መለየትን ወዘተ. የሚመለከት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአንብቦ መረዳት ንኡስ ክሂል ቃላት እና ሀረጋትን የመረዳት ክሂል ነው፡፡ የቃላት እና የሃረጋትን ትርጉም በጽሁፍ ውስጥ በግልጽ ከሰፈሩ መረጃዎች እና ፍንጮች በመነሳት ወይም ከቀደመ እውቀት በመነሳት ወይም ሁለቱን በማቀናጀት የመረዳት አቅምን የማጎልበት ሂደት ነው፡፡ ለዚህም የቃላት እና የሃረጋትን ቀጥተኛ ትርጉም ከመረዳት ባሻገር አውዳዊ ፍቻቸውንም መረዳት ይጠበቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለአንብቦ መረዳት መሰረታዊ የሆኑትን ፈሊጦች፣ ዘይቤዎች እና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ከገቡበት አውድ አንጻር መተረጎም እና መረዳትም ትልቁ ክህሎት ነው፡፡ እንዲሁም የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች የንባብ

ስልት ሲሆኑ እነዚህም የገረፍታ ንባብ፣ የአሰሳ ንባብና ጥልቅ ንባብ የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህን ስልቶች ጠንቅቆ በማወቅ በንባብ ጊዜ እነደአላማችን በመቀያየር የመጠቀም ልምድን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡

Ur, P. (1996፡148) አንብቦ መረዳት ሲባል በጽሁፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት በተቻለ መጠን የመገንዘብ ሂደት ሲሆን ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው በቀላሉ እንዲረዱ የሚቀርበው ምንባብ የቋንቋ ይዘት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ከግንዛቤ ያስገባ መሆን ይኖርበታል ይላሉ፡፡ በተጨማሪም Alderson እና Urquhart (1984፡65) ሃሳባቸውን ሲገልጹ ‹‹የአንብቦ መረዳት ትምህርት የተመለከተን ግብ እንዲመታ መምህሩ በቅድሚያ የቀረበው ምንባብ ከተማሪዎች እውቀት እና ክህሎት እንዲሁም ማህበራዊ ዳራ ጋር የሚጣጣም መሆኑን መፈተሽ አለበት›› ሲሉ ይመክራሉ፡፡ በመሆኑም አንድ መምህር እነዚህን ጉዳዮች በቅድሚያ ከፈተሸ እና ካስተካከለ በኋላ አንብቦ መረዳትን በክፍል ውስጥ ማስተማር ይችላል፡፡ ትምህርቱም በሚከተሉ መንገዶች መሰጠት እንዳለበት Harmer (1991፡182-184) እና Grellet (1981፡4-5)እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፡፡

- የቃላት ፍቺን ማንበብ፡- ተማሪዎች በምንባቡ የቀረቡትን ቃላት አውዳዊ እና አገባባዊ ፍቻቸውን እንዲረዱ ማድረግ ይገባል፡፡ የቃላት ፍቺ ሲባል የእያንዳንዱን ቃል ተናጥላዊ ፍቺን ለቅሞ ማስረዳት ሳይሆን የህብረት ፍቺ የማስረዳት ሂደት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡
- የምንባቡን ግልጽ መልዕክት ማስገንዘብ፡- ይህም ሲባል በጽሁፍ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልእክት ለማብራራት እና ለማጉላት፣ አጽዕኖት ለመስጠት የገቡትን የተለያዩ ሀሳቦችን ማስገንዘብን ይመለከታል፡፡
- የምንባቡን ድብቅ መልዕክት ማስረዳት፡- ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልእክት መነሻ በማድረግ በአንድምታ የተቀመጠውን ወይም ድብቁን መልእክት እንዲረዱ ማድረግ ይመለከታል፡፡
- የምንባቡን ሀሳብ ፍሰት ማስገንዘብ፡- ተማሪዎች የምንባቡን ቅደም ተከተል፣የሀሳብ ፍሰት፣ የሀሳቦችን ቅንብር እና ዝምድና መገንዘብ ይገባቸዋል፡፡ይኸውም በአረፍተነገሮች እና አንቀጾች ቅደም ተከተላዊ ውህደት እና ዝምድና ሊገለጽ ይችላል፡፡
- አያያዥ ቃላት እና ሀረጋትን ሰዋሰዋዊ አገባብ እና ትርጉም ማስገንዘብ፡- ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የሚያገኙትን አያያዥ ቃላት እና ሀረጋት ያላቸውን ሰዋሰዋዊ አገባብ እና ትርጉም ማወቃቸው የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ በቀላሉ እንዲገነዘቡ ያግዛቸዋል፡፡

ማስተዋል (1989፡8-9) Grellet (1981፡4-5)፣ Greenwood (1981፡89) እና Ellis (1980፡ 141-142)ን ጠቅሰው እንደሚያብራሩት አንብቦ መረዳት ማለት በጽሁፉ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነው፡፡ ዘርዘር ተደርጎ ሲታይም አንብቦ መረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል በማለት ይዘረዝሯቸዋል፡፡

**ሀ. የቃላትን ፍቺ መገንዘብ፡-** አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አውዳዊ ፍቺ ሊረዳ ይገባዋል፡፡ ይሁን እንጂ የጽሁፉን መልእክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ማወቅ የግድ አስፈላጊ ስላልሆነ አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት ፍቺዎች አንድ በአንድ መመርመር አይጠበቅበትም፡፡

**ለ. የጽሁፉን ግልጽ መልእክት መገንዘብ፡-** አንባቢው በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልእክትና ይህን መልእክት ለማጉላት ሆነ ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ሀሳቦች መረዳት አለበት፡፡

**ሐ. የጽሁፉን ውስጣዊ (ድብቅ) መልእክት መገንዘብ፡-** በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ የቀረበውን መልእክት መገንዘብ አንብቦ የመረዳት ዋነኛ አካል ቢሆንም አንባቢው በዚሁ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም፡፡ በግልጽ የተቀመጠውን መልእክት መነሻ በማድረግ በማገናዘብና በመመርመር የሚደረስበትን ውስጣዊ መልእክትም መረዳት ይጠበቅበታል፡፡

**መ. የአያያዦችን ሰዋሰዋዊ አገባብና ትርጉም መገንዘብ፡-** አንድ አንባቢ በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙትን አያያዦች አገባብ፣ አገልግሎት እና ትርጉም መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህን መገንዘቡ የጽሁፉን መልእክት ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክትለታል፡፡

**ሠ. የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ የሃሳብ ፍሰት መገንዘብ፡-** አንባቢው ጽሁፉ ውስጥ ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ተናጥላዊ መልእክት መረዳቱ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገርም የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ ሃሳብ አገላለጽ፣ ዓ.ረፍተ ነገር ከፊተኛው እና ከተከታዮቹ ዐረፍተ ነገሮች ጋር ያለውን የሃሳብ ግንኙነት ፣ የጽሁፉ የተለያዩ አንቀጾች ያላቸውን የእርስበርስ ግንኙነት ሊረዳ ይገባዋል፡፡

ከምሁራኑ አገላለጽ የምንረዳው የአንድን ጽሁፍ መልእክት አንብቦ ለመረዳት የቃላት ፍቺን መገንዘብ ፣ የጽሁፉን ግልጽ መልእክት፣ የጽሁፉን ውስጣዊ( ድብቅ) መልእክት ፣ የአያያዦችን

ሰዋሰዋዊ አገባብና ትርጉም እንዲሁም የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ የሃሳብ ፍሰት መገንዘብ እንዳለብን እና አጠቃላይ እነዚህን ተግባራት መፈጸም እንዳለብን ነው፡፡

## 2.2 የማንበብ ብልሃት ምንነት

ብልሃት የሚለው ጽንሰሃሳባዊ ቃል የመማር ባህሪ፣ እቅድ፣ ዘዴ ወዘተ. በሚሉ ተቀራራቢ ትርጉም ባላቸው ቃላት ይገለጻል፡፡ ማንበብ ብልሃት ወጥ የሆነ ብያኔ ባይኖረውም ምሁራን ግን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ Anderson (1991) እንደሚገልጹት ደግሞ የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች አዲስ መረጃን ለማግኘት እና ያገኙትን መረጃ ወደራሳቸው መረጃ አሻሽለው እና አስተካክለው ለማቅረብ (ለመጠቀም) የሚያስችላቸው አእምሯዊ ተግባር ነው፡፡

Rubin (1975፡45) የቃሉን ጽንሰሃሳብ ሲበይኑ ተማሪዎች አዲስ እውቀትን ለማግኘት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው በማለት ሲገልጹ O, Malley (1985፡23) እንደሚሉት ቋንቋ የመማር ብልሃት ተማሪዎች መረጃን ለማግኘት፣ ለማጠራቀምና ዳግም ለመጠቀም የሚያስችላቸው አእምሯዊ ተልእኮ ቅደም ተከተል ነው ይላሉ፡፡

እንደ Cubuku (2007፡95) አገላለጽ ብልሃት ሰዎች ተግባራትን ለመገንዘብና ለመተግበር የሚያቅዱት እቅድ ነው፡፡ ብልሃት ሰዎች የመማር ባህሪያቸውን በሚያቅዱበት እና በሚገመግሙበት ወቅት እንዴት እንደሚያስቡ እና እንደሚተገብሩ ለማሰብ ያስችላቸዋል፡፡

Bolck (1986፡465) እንደገለጹት የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የተሰጠን የማንበብ ተግባር ለመረዳት በንቃተህሊና ሆን ብለው የሚጠቀሙበት ዘዴ፣ የአዕምሮ ተልኳዊ አሰራር ወይም ቅደምተከተል ሆኖ ተማሪዎች ውህድ አሀዱን ለመረዳት ምንአይነት ምልክት(ፍንጭ) እንደሚጠቀሙ ፣ ያነበቡት እንዴት ስሜት እንደሚሰጥ ፣ ባልገባቸው ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመገንዘብ እርምጃ የሚወስዱበት መሳሪያ(መንገድ) የማንበብ ብልሃት ነው፡፡ Phakiti (2006፡23) በበኩላቸው እንደገለጹት የማንበብ ብልሃት አንባቢዎች በማንበብ ሂደት የቀረበላቸውን ጽሁፍ አንብበው ለመረዳት በንቃተህሊና ሆን ብለው እና አስበውበት የሚተገብሩት ግብ ተኮር እቅድ ነው ይባላሉ፡፡

እሱባለው(2010) የማንበብ ብልሃት ሆን ተብሎ የሚተገበር፣ ቅደም ተከተላዊ አላማ ተኮር ፣ ትጋት የሚፈልግ፣ ፈቃደኝነትን የሚሻ፣ በጣም አስፈላጊ እና የማንበብ ሂደትን አመቻች ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የማንበብ ሂደታቸውን በማመቻቸት አንብቦ መረዳታቸውን ለማጎልበት

እንዲሁም የሚያጋጥሙ ችግሮችን በማስወገድ የተለየ የማንበብ ግባቸውን ለማሳካት ሆን ብለው የሚተገብሩት አእምሯዊ ክንውን ነው፡፡እንዲሁም Davies (2011) እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የማንበብ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ አንባቢዎች ጽሁፍን በንቃት ተከታትለው በማንበብ እንዲረዱና ባልተረዱ ጊዜ ምንማድረግ እንዳለባቸው የሚያግዙ ናቸው፡፡

Ephrem (2009) Foley (2011)ን ጠቅሰው እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የየራሳቸው መጠሪያና ምንነት ቢኖራቸውም ለአንብቦ መረዳት ትምህረቱ በተናጥል የሚቆሙ አይደሉም፡፡ ይልቁንም ርስበርሳቸው የተሳሰሩና የሚገነባቡ ናቸው፡፡ አንባቢዎች የብልሃቶችን ምንነትና አጠቃቀም ማወቃቸው በቅድመ ንባብ፣ በንባብና በድህረንባብ ጊዜ ትምህርቱን ለመከታተልና ተግባራቱን ለማከናወን ፍላጎት እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል፡፡

Nga (2007) ጥናት በአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ላይ በማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን ጥናቱ የተካሄደበት አገር ቬተናም ውስጥ በሚገኝ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት የሚገኙ መምህራን ተሳታፊ ያደረገ በመሆኑ ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ከተካሄደበት ሀገርና የጥናቱ ትኩረት አንጻር ይለያል፡፡እነዚህ ልዩነቶችም ለዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ሌላው ከአጥኚው ርዕስ ጋር በተዛማጅነት ሊጠቀስ የሚችለው የእንደሪስ (2000) ጥናት ሲሆን ጥናቱ በአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ቢመሳሰልም በሌላ መልኩ ግን በሰፊው ይለያል፡፡ይህ ጥናት የ9ኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን የሚመለከት ሲሆን የእንድሪስ ጥናት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መማር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በሙከራዊ ጥናት የተካሄደ ነው::

## 2.3 የማንበብ ብልሃት ጠቀሜታ

እንደ Cubukcu (2007፡95) አገላለጽ የማንበብ ብልሃት አጠቃለይ እውቀት እና ጥልቅ (ዝርዝር) መረጃ ለማግኘት፣ዋናውን ሃሳብ (ጭብጥ) ለይቶ ለማውጣት፣ ለመማር፣ ለማስታወስ፣ ደስታን ለመፍጠር፣ ጭምቃሃሳብ ለመጻፍ እና ምርምር ለመስራት ይጠቅማል በማለት ይገልጻሉ፡፡

Mokhtari & Reichard (2002) እና Pressley (2002) የማንበብ ብልሃት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይጠቅሳሉ፡፡ እነሱም የበለጠ እራሳቸውን የቻሉ ራስመር (selfe-

regulted)፣ ነጻ (Autonomous)፣ እና ግለብቃታቸው ከፍ ያለ እንዲሆን እምነት ያለቸው (Self-efficacy)፣ ለትምህርት ሃላፊነት የሚወስዱ ጠንካራ አንባቢዎች እንዲሆኑ፣ የማንበብ ብልሃቶችን በሚገባ በመጠቀም አንብቦ የመረዳት ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ፣ የሚያነቡትን የሚገነዘቡ በመሆናችው ሁልጊዜ ለመማር የተነሱ ንቁ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች በንቃት የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚከታተሉ በመሆናቸው ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

Middleton (1989) እንደሚሉት ከሆነ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መጠቀም ለቀረበው ጽሁፍ የተደራጀ መልዕክት የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣ ያገኙትን መረጃ በአዕምሮ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ለማቆየት፣ አዕምሯዊ ችሎታን ከፍ ለማድረግ እና አገናዛቢነትን ለማዳበር ይረዳል፡፡

Mc,Namara (2007፤34) ስለማንበብ ብልሃት ጠቀሜታ ሲያብራሩ በማንበብ ሂደት ተማሪዎች የተለያዩ ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡ ከሚገጥሟቸው ችግሮች የተወሰኑት በአረፍተነገር ውስጥ ያሉ ቃለት በአንድነት ሆነው እንዴት ትርጉም እንደሚሰጡ የመረዳት ችግር፣ እያንዳንዱን ቃላት ወይም አረፍተነገር በነጠላ ቢረዱም በአረፍተነገሮቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም በአጠቃላይ የውህድ አሀዱን ፍቺ አለመረዳት፣ የጽሁፉን ዘውግ አለመረዳት፣ እውቀት የሚጠይቁ ውህድ አሃዶችን የመረዳት ብቃት ማነስ ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የማንበብ ብልሃቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ነው ይላሉ፡፡

## 2.4 የማንበብ ብልሃት አይነቶች

የማንበብ ብልሃት አይነቶችን የተለያዩ ምሁራኖች በተለያየ መልኩ ቢከፍሏቸውም እሱባለው(2010) oxford (1990)ን በመጥቀስ በአምስት ይከፍላቸዋል፡፡

### 1. አእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት

አእምሮታዊ ማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የቀረበውን ጽሁፍ በራሳቸው ለማንበብ፣ ተግባራትን ለመጨረስ እና ወደፊት ለመገስገስ፣ የሚማሩት ትምህርት እንዲገባቸው፣ በማንበብ ወቅት የሚገጥማቸውን ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ እንዲሁም በማንበብ ሂደት ከእንዳንዱ የማንበብ ችግር ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ጽሁፍን ለማብላላት፣ ለመረዳት፣ ለመተንተን ሲባል የሚተገበር ነው፡፡

## 2. ልዕለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት

ልዕለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት በማንበብ ሂደት ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ራስን እና አንብቦመረዳትን ለመቆጣጠር እንዲሁም የመማርን ክንውን ውጤታማነትን ለመገምገም የሚያስችል ከፍተኛ ደረጃ የማስተዳደር ክሂል ነው። እንዲሁም ልዕለአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች የራሳቸውን የማንበብ ሂደት እና አእምሯቸውን ለመቆጣጠር ሆን ብለው የሚተገብሩት በግልጽ የማይታይ ባህሪ ነው።

## 3. ትውስታ የማንበብ ብልሃት

ይህ የማንበብ ብልሃት አንድ ጊዜ ለትውስታ የሚረዳ ተብሎ ይጠራል። በትውስታ ብልሃት አጠቃቀም መረጃን ማጠራቀምና ያጠራቀሙትን መረጃ እንደገና መጠቀም ወሳኝ ጉዳይ ነው። የብልሃቱ ዋነኛ መርህ ተማሪዎች እውቀታቸውን ለማዳበር ያነበቡትን ጠቃሚ ሃሳብ ማስቀመጥና አስታውሶ እንደገና መጠቀም ነው።

## 4. ማካካስ የማንበብ ብልሃት

ማካካሰስ የማንበብ ብልሃት ተማሪዎች አነስተኛ እውቀት ቢኖራቸውም አዲስ ቋንቋን ለመረዳት ወይም ለማፍለቅ ይረዳቸዋል። ይህ ብልሃት በታላሚው ቋንቋ የሰዋሰው እና የቃላት ማነስን የማስተካከል እቅድን ለማሳካት የሚያገለግል ብልሃት ነው።

## 5. ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት

ማንበብ ግለሰባዊ ቢሆንም የተነበበውን የበለጠ ለመረዳት የሰዎችን ተግባራዊ ተሳትፎ ይፈልጋል። ተግባቦትም በሰዎች መካከል የሚፈጠር መስተጋብር ነው። በማንበብ ሂደት ደግሞ የሰዎች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ተገቢ ማህበራዊ ብልሃት መጠቀም ጠቃሚ ነው። በማህበራዊ ብልሃት ስር የሚካተቱት ንኡሳን ብልሃቶች ጥያቄ መጠየቅ፣ ከሌሎች ጋር መተባበር እና ሌሎችን ማዳመጥ የሚሉት ናቸው።

## 2.5 በብልሃቶች አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች

ተክላይ (2000፡29) Ellis (1994፡543)፣ Wenden (1991፡35-36) እና Wallace (1992፡42)ን ጠቅሰው እንደሚያብራሩት በብልሃቶች አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች በርካታ ቢሆኑም በዋናነት አምስቱን እንደሚከተለው ይገልጽዋቸዋል፡፡

### ሀ. የቋንቋ ሁኔታ

በቋንቋ ሁኔታቸው ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች ውጤታማ ካልሆኑ ተማሪዎች በርካታና የተለያዩ የንባብ ብልሃት አይነቶችን በተሻለ ደረጃ እንደሚጠቀሙ Brhanu (1993፡71) ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም በቋንቋ ችሎታው የተሻሉ ተማሪዎች በኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶች አጠቃቀማቸው የተሻሉ ናቸው (Ellis 1994፡541)፡፡

### ለ. የትምህረት ደረጃ

Ellis (1994) Ehrman (1990)ን ተቅሰው እንደገለጹት የተማሪዎች የትምህርት ደረጃ እና የብልሃቶች አጠቃቀም የተቆራኙ ናቸው ብለዋል፡፡ ይሄውም ስልጠና ከሌላቸው መምህራን እና ተማሪዎች ይበልጥ የስነልሳን ባለሙያዎች የሆኑት ብዛት ያላቸው ብልሃቶችን በተደጋጋሚ ሲጠቀሙ ተስተውለዋል፡፡

### ሐ. የምንባብ አይነት

የንባብ ብልሃቶች እንደየምንባቡ ባህሪይ ወይም ዓይነት ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ፡-ቀጥተኛ፣ ፈጣን እና ተመስጣአዊ ብልሃቶች ከተራኪ ድርሰት ምንባባት ጋር ሲቆራኙ ልምምዳዊ ብልሃቶች ደግሞ ከአስረጅ ድርሰት ምንባባት ጋር ይቆራኛሉ (Wallace 1992፡57)፡፡

### መ. ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶች

ቀጥተኛ ብልሃቶች አብዛኛውን ጊዜ ከተወሰኑ የመማር ተግባራት እና ከተወሰኑ የመማር ዓላማዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሲኖራቸው፣ ኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶች ግን በሁሉም የመማር ተግባራት ላይ አንድ አይነት ናቸው ለማለት ይቻላል (Chamot 1987፡72)፡፡

### ሠ. የንባብ ብልሃት ዓይነቶችና ቅንጅታቸው

አንብቦ መረዳትን የሚያግዙ ውጤታማ እና ውጤታማ ያልሆኑ የንባብ ብልሃት አይነቶች እንዳሉ የሚያምኑ የመስኩ ባለሙያዎች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል Bolck (1986) ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል በመሰረቱ ‹‹ብልሃቶችን ውጤታማ እና ውጤታማ ያልሆኑ በማለት መክፈል አይቻልም›› የሚሉ ወገኖችም አሉ፡፡ ከነዚህ መካከል Davies (1995፡47) ይገኙበታል፡፡ በሌላ መልኩ Davies (1995) የንባብ ብልሃት አይነቶች ውጤታማ የሚሆኑት ከሌሎች የንባብ ብልሃት አይነቶች ጋር ባላቸው ቅንጅት ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

## 2.6 ማንበብን ማስተማሪያ ዘዴ

እንደ ዘውዱ (2008፡33-35) ገለጻ የማንበብን ክሂል ለማስተማር በተለያዩ ጊዚያት የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንበቡ እና ጥያቄዎችን መልሱ (read and do) የሚለው የተለመደው ማንበብን ማስተማሪያ ዘዴ (Regular Reading Instruction) ብዙ አመታትን ያስቆጠረ እና አሁንም እየተሰራበት ያለ ነው፡፡ በምርምር ላይ ከተመሰረቱት እና እ.አ.አ ከ1980ቹ ወዲህ በተግባር ላይ ከዋሉት ዋና ዋና ማንበብን ማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ የተለመደው የማንበብ የማስተማሪያ ዘዴ እና ሚና ለዋጭ ዘዴ ይጠቀሳሉ፡፡

### 2.6.1 የተለመደው የማንበብ የማስተማሪያ ዘዴ

የተለመደው የማንበብ የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን በማስተማር ተማሪዎች ደግሞ በመማርና በመለማመድ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ በዚህ ዘዴ መምህራን ተማሪዎችን በማስተማር የላቀ ሚና ያላቸው ሲሆን ተግባሩም በሁለት የተከፈለ ነው፡፡ መምህራን ያስተምራሉ፡፡ ተማሪዎች ይማራሉ፤ ይለማመዳሉ Panmanee (2009)፡፡

እንደ Panmanee (2009) እና Seid (2012) አገላለጽ የተለመደው የቡድን የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ምንባቡን ማስተዋወቅ፣ በምልከታ በአሰሳ ጽሁፍን መቃኘት፣ ምንባቡን በግል ማንበብ፣ በምንባቡ ላይ መወያየት፣ በተደጋጋሚ ለሚቀርቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መልስ መስጠት በሚሉት ተግባራት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ዘዴ የመምህራን ዋና ዋና ተግባራት በሚቀርበው ርእስ  ላይ ቀጥተኛ ገለጻ ማድረግ እና የተማሪዎችን ተግባራት መቆጣጠር ናቸው፡፡በልምምዱ መጀመሪያ መምህራን

ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ ወይም ከምንባቡ ርእሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅ የሆነ ታሪክ (ጽሁፍ) በማንበብ ዳራዊ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ ይሞክራሉ። ይህም ወደ ማንበቡ ተግባር እንዲገቡ ያግዛቸዋል፡፡ከዚያም መምህራን በርእሰ ጉዳዩ ላይ ገለጻ ያደርጋሉ ወይም ትክስቶቹን ይተገብራሉ። በቴክስቶቹ መሰረትም ተማሪዎች የጽሁፉን ዋና ሀሳብ እና ዝርዝር ሀሳብ ይለያሉ፤በጽሁፉ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ወይም ያልተለመዱ ቃላትን እና ሀረጋትን ትርጉም ይገምታሉ፤ የጥቆማን ወይም የአንድምታን ስልት ይጠቁማሉ።

ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ሆነ መልመጃዎችን በሚሰሩበት ጊዜ መምህራን ለተማሪዎች ጥያቄ በማቅረብ ወይም ታሪክ በመንገር ዳራዊ እውቀታቸውን ያነቃቃሉ፤ ቀጥተኛ ገለጻ በማድረግ ያስተምራሉ፤ቴክኒኮቹንም ሞዴል ሆነው ያሳያሉ። ከዚያም ተማሪዎች ጽሁፉን ያነባሉ፤ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን በመለየት፣ የአዳዲስ ቃላትንና ሀረጋትን ትርጉም በመገመት፣ የጥቆማን ወይም የአንድምታን ስልት በመጠቀም የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን ጥያቄዎች ይመልሳሉ። መምህራንም የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ይፈትሻሉ፤ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ።

## 2.6.2 ሚና ለዋጭ ዘዴ (Reciprotical Teaching)

ሚና ለዋጭ ዘዴ በመምህር እና በተማሪ፣ በተማሪ እና በተማሪ መካከል ምልልስ በመጠቀምና አእምሯዊ ብልሃቶችን በመተግበር የአንድን ጽሁፍ ከፊል ወይም ሙሉ ክፍል ለመረዳት የሚከናወን ሂደት ነው።

ሚና ለዋጭ ዘዴን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቁት Palincsar እና Brown (1984) ናቸው። ተመራማሪዎቹ ይህን ዘዴ ሲመሰርቱ ዓላማ አድረገው የተነሱት የድምጽንና የፊደልን ግንኙነት መለየት (decoding) የሚችሉ ነገር ግን አንብቦ መረዳት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ወይም ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ ነው። በዚህ ዘዴም በመጀመሪያ በመምህርና በተማሪ የሚና ልውውጥ ይደረጋል። በመቀጠልም ተማሪዎች ሚና በመለዋወጥ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ። ሚና ላወጭ ዘዴ ከሚያቅፋቸው ከመገመት፣ ከመጠየቅ፣ ከመብራራት እና ከማጠቃለል አእምሯዊ ብልሃቶች እንደያዙት ሚና ተግባራቸውን በማከናወን የሚመደበው ክፍለጊዜ እስኪጠናቀቅ ትብብራዊ በሆነ መንገድ እንደገና የሚናልውጠቱ በአራቱም አእምሯዊ ብልሃቶች ላይ ይቀጥላል።

ሚና ለዋጭ ዘዴ በምልልስ ሂደት ላይ የተመሰረተ የትምህርት አቀራረብ ነው። በምልልስ ላይ የተመሰረተውም በሁለት ምክንያቶች እንደሆነ Polincsar እና Browen (1984) ይገልጻሉ። አንደኛ ተማሪዎች እንግዳ ባልሆኑበት ቃላዊ ወይም ቋንቋዊ ቅጽ (language format) ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም ከማንበብ ጋር ለሚታገሉ ተማሪዎች ከባድ ከሆነው ከመጻፍ ተግባር የቀለለ ሊሆንላቸው ይችላል። ሁለተኛው መምህራን ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ስርአታዊ እና አላማ ተኮር በሆነ መንገድ ለመከታተል ወይም ለመቆጣጠር ያስችላል።

Blazer (2007) ሚና ለዋጭ ዘዴን ሲገልጹት የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት የሚያሳድግ፣ በራስ መተማመናቸውን እና ተነሳሽነታቸውን የሚጨምር፣ በሁሉም የክፍል ደረጃዎችና በማንኛውም የትምህርት አይነት ጽሁፍን ለመረዳት ወይም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችግር ለመቅረፍ የተቀረጸ የተምህርታዊ አቀራረብ (structional approach) ነው ይላሉ። እንዲሁም ተማሪዎች የመገመት፣ የመጠየቅ፣ የማብራራት እና የማጠቃለል አእምሯዊ ብልሃቶችን በመማር ከአንድ ጽሁፍ ትርጉም የመመስረት ችሎታቸውን የሚያሳድጉበትና የመረዳት ሂደታቸውን የሚቆጣጠሩበት ዘዴም ነው። ዘዴው እነዚህ አራት አእምሯዊ ብልሃቶችን መሰረት ያደረገ ነው።ብልሃቶቹም ጽሁፉን ለመረዳት የሚተገበሩ አእምሯዊ ክንዋኔዎች ናቸው። Lubliner (2001) እንደሚገልጹትም ሚናለዋጭ ዘዴ ከማንበብ ፈተና ጋር የተያያዘ የአንበብቦ መረዳት ውጤትን ለማሻሻል ብቻ ሳይሆን ዘላቂነት ያለው የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሻሻል የሚያስችል ውጤታማ ዘዴ ነው ይላሉ።

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በጉመር ወረዳ ከሚገኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መካከል በተመረቱ ትምህርትቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአንብቦ መረዳት ብልሃት የክፍል ውስጥ አተገባበር መፈተሸ ላይ ያተኩራል፡፡

በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አንብቦ መረዳት ብልሃት ያለቸውን ግንዛበቤ እና አተገባበር በተመለከተ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ዝርዝር መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃት የክፍል ውስጥ አተገባበር ትክክለኛ መረጃ ተሰንዶ በገለጭ የምርምር አይነት ተጠንቷል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ተሳታፉዎች

በዚህ ጥናት አካላይ የሆኑት በጉመር ወረዳ ከሚገኙት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መካከል በተመረጡ ሁለቱ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ ትምህርትቤቶች በምቾት ናሙና ተመርጠዋል፡፡ምክኖያቱም በወረዳው ውስጥ ያሉት ትምህርትቤቶቹ ያሉበት ቦታ የተራራቁ መሆናቸውና መረጃ ለመሰብሰብ ከጊዜም ከገንዘብም አንጻር አስቸጋሪ በመሆኑ በምቾት ናሙና መሰረት ለአጥኚው አመቺ የሆኑትን ትምህርትቤቶች ተመርጠዋል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት የተሳተፉ መምህራን በጀንቦሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና አረቅጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በጥናቱ ተካተዋል፡፡የመምህራኑም የትምህርት ደረጃ አራቱ የመጀመሪያ ዲግሪ ሲሆኑ ሁለቱ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡

### 3.2.2 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

ይህ ጥናት የተተገበረው (የተካሄደው) በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ ካሉት አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ማለትም በጀንቦሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በአረቅጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ትምህርት ቤቶቹም በአመቺነት ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ትምህርትቤቶቹም የተመረጡበት ምክንያት ለአጥኚው ካላቸው የቦታ ቅርበት እና አመቺነት አንጻር መረጃን በቀላሉ ለመሰብሰብ ስለሚያስችሉ ነው፡፡

### 3.2.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ዘጠነኛ ክፍል በኢላማዊ ንሞና ዘዴ የተመረጠ ሲሆን ይህ ክፍል ደረጃ የተመረጠበት ምክንያት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እርከን ትምህርት ተጠናቆ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እርከን ሽግግር የሚደረግበት በመሆኑና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መነሻ በመሆኑ እንዲሁም በዚህ ደረጃ ያለውን የአንብቦ መረዳት ሁኔታ እና የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን በጥልቀት ለመመርመር ነው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት እንዲውሉ የተደረጉት መረጃ መሰብሰቢያዎች ሁለት ሲሆኑ እነሱም ጽሁፍ መጠይቅ እና ምልከታ ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተመረጡት የጥናቱን አላማ እና አጠናን ዘዴን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በመቀጠልም የእያንዳንዱን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ተግባር በዝርዝር እናያለን፡፡

### 3.3.1 ምልከታ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበር መመርመር ሲሆን ለዚህ ጥናት እንደዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተመረጠው ምልከታ ነው፡፡ ይህም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው በክፍል ውስጥ በመገኘት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች በመከታተል አሳማኝ የሆኑ መረጃዎችን ለማሰናዳት ስለሚያስችለው ነው፡፡ አጥኚው ምልከታውን ከማድረጉ በፊት መምህራንን ፈቃደኝነታቸውን የጠየቀና የሚከታተልበት ቅጽ ያዘጋጀ ሲሆን የምልከታ ቅጹም አንብቦ መረዳት ብልሃቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበር ሁኔታን ለመመርመር ያስችሉኛል ያላቸውን 32 ተግባራትንና የትግበራውን

መጠን የሚገልጹ ከፍተኛ(4)፣ መካከለኛ(3)፣ ዝቅተኛ(2) እና በፍጹም(1) በሚሉ አራት ደረጃዎች ከፋፍሎ አዘጋጅቷል፡፡

### 3.3.2 የጽሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የጽሁፍ መጠይቅ ጥቅም ላይ ሊውል የቻለበት ዋና አላማ አጥኚው በምልከታ ወቅት ከሰበሰበው መረጃ በተጨማሪ ያላገኛቸውን መረጃዎች በጥናቱ ውስጥ ለማካተት እና በምልከታ ካገኛቸው መረጃዎች ጋር ለማመሳከር ስለሚያስችለው ነው፡፡በተጨማሪም ጽሁፍ መጠይቅ የተመረጠበት ምክንያት ተጠኚዎቹ ሀሳባቸውን በነጻነት ለመግለጽ ስለሚያስችላቸው ነው፤ ለአጥኚውም ቢሆን ካለው የጊዜ እጥረት እና የሁኔታዎች አለመመቻቸትን በተወሰነ መልኩ ያቃልላል በሚል ነው፡፡የጽሁፍ መጠይቁ ቅጽ ተዘጋጅቶ ለተጠኚዎቹ ከመሰጠቱ በፊት አጥኚው የጥናቱን አላማ በማስረዳትና በነሱም ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

## 3.4 የአጠናን ሂደት

በመጀመሪያ አጥኚው በዚህ ርእስ ላይ ጥናት እንዲያደርግ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጸድቆለት የድጋፍ ደብዳቤ የተሰጠው በመሆኑ በትንህርት ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች እውቅና አግኝቷል፡፡ በመቀጠልም መጠይቆቹን የማዘጋጀትና የማስገምገም ሲራ ተግብሯል፡፡እንዲሁም

በጉመር ወረዳ ከሚገኙ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በ4 ትምህርትቤቶች ውስጥ ለሚሰሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መረጃ እንዱሰጡት ፈቃደኝነታቸውን ጠይቋል፡፡ እንዲሁም በተመረጡ 4 ወንድ 2 ሴት በጥቅሉ 6 ያማርኛ ቋንቋ መምህራንን በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በመቸረሻም የተሰበሰቡት መረጃዎች በማደራጀት የውጤት ትንተናውን አድርጓል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት ዋና አላማው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ሲሆን ጥናቱም በቅይጥ የምርምር መተንተኛ ዘዴን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ጥናት ይዞት የተነሳውን አላማ ከግብ ለማድረስ ለመረጃ መሰብሰቢያነት በተመረጡት ምልከታ እና ጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኙትን መረጃዎች በቅይጥ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

ይህም ምዕራፍ በጥናቱ የተካተቱት ከጉመር ወረዳ የተመረጡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአንብቦ መረዳትየክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስልየተሰበሰቡ መረጃዎች የውጤት ትንተና ማብራሪያ የሚቀርብበት ምዕራፍ ነው፡፡

## 4.1 የውጤት ትንተና

ይህ ጥናት መሰረት አድርጎ የተነሳው በጉመር ወረዳ በሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ የተኮረ ሲሆን በዋናነት ሊመልሳቸው የሚገቡ ጥያቄዎች ብሎ ያነሳቸውም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን አተገባበር ያላቸውን ግንዛቤ መፈተሽ? የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበበራቸውን መቃኘት እና በመምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተግዳሮቶችን መለየት የሚሉ ናቸው፡፡

በቅድሚያ ጥናቱ እንዲመልስ ይዞት የተነሳው የመጀመሪያው መሰረታዊ ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ ያደርጋሉ? የሚል ሲሆን ይህን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠትና ለማብራራት ከመረጃ መሰብሰቢያ ውስጥ አንዱ በሆነው በምልከታ የተገኘውን መረጃ በአይነታዊ በመጠናዊና ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ይህንንም ለማድረግ የመገምገሚያ ቅጽ አዘጋጅቶ በማቅረብና ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ማለትም ስድስቱም መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት በክፍል ውስጥ በመገኘት በእያንዳንዳቸው አራት አራት ክፍለ ጊዜ ምልከታ በማካሄድ እና የተገኘውንም መረጃ አማካዩን በመስራት ነው፡፡ ከዚያ በመቀጠልም የሁሉም መምህራን አጠቃላይ የ24 ክፍለ ጊዜ የምልከታ ውጤት አማካይ በመቶኛ በማስላት የእያንዳንዱ ብልሃት አተገባበር ደረጃ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጭራሽ በሚሉት ስር ተመድበው ተቀምጠዋል፡፡

## 4.1.1 በ2ቱ ትምህረትቤቶች የተካተቱ መምህራን ምልከታ የተገኘው ውጤት ትንተና

### ሠንጠረዥ 4.1.1.1 የቅድመ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን አንጻር ሲተነተን

| ተ.ቁ | ቅድመ ንባብ ብልሃቶች | የአተገባበር ሁኔታ አማካይ በመቶኛ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጭራሽ |
| 1 | የምንባብ ሀሳብ መገመት | | | | |
| 1.1 | ተማሪዎች የምንባቡን ርዕስ ተመልክተው ምንባቡ ስለምን ሊያስገነዝብ እንደሚችል ቀድመው እንዲገምቱ ማድረግ | 8.4 | 15.6 | 40.7 | 35.3 |
| 1.2 | ተማሪዎች ሠንጠረዡንና ሌሎች ሁኔታዎችን ተመልክተው የምንባቡን ጭብጥ/ ይዘት እንዲገምቱ ማድረግ | 4.7 | 9.2 | 51.8 | 34.3 |
| 2 | የቀደመ እውቀት መቀስቀስ | | | | |
| 2.1 | ተማሪዎች ንኡሳን ይዘቱን ከቀረበው ምንባብ ላይ ተነስተው ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ማድረግ | 6.3 | 11.4 | 58.4 | 23.9 |
| 2.2 | በርእሱና በንኡሳን ይዘቱ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲያንጸባርቁ ማድረግ | -- | - | 51.2 | 48.8 |
| 2.3 | ተዛምዶ ያላቸውን ቃላት፣ አባባሎችና ጽንሰሀሳቦች ከሚነበበው ጽሁፍ ጋር ያላቸውን ቁርኝነት በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ | 12.7 | 23.2 | 46.5 | 17.6 |
| 3 | ምስል መፍጠር/መገንባት | | | | |
| 3.1 | ተማሪዎች ንኡስ ይዘቱን፣ ሰንጠረዥና ሌሎች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ምንባብ ይዘት በአእምሯቸው ምስል መፍጠር እንዲችሉ ማገዝ | - | 24.4 | 42.4 | 33.2 |
| 4 | የመምህሩ ሞዴል መሆን፣ማበረታታት፣ ድጋፍ ማድረግ፣ ግብረ መልስና ማጠቃለያ መስጠት | | | | |
| 4.1 | ውጤታማ ብልሃቶችን ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሞዴል መሆን | 6.9 | 19.3 | 27.7 | 46.1 |
| 4.2 | አስፈላጊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | 11.4 | 38.2 | 29.4 | 21 |
| 4.3 | ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉትን ተማሪዎች ማበረታታት | 7.5 | 34.3 | 39.5 | 18.7 |
| 4.4 | አስፈላጊ የሆነ ማስተካከያና ግብረ መልስ መስጠት | 9.8 | 43.3 | 20.2 | 26.7 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ 4.1.1.1 እንደሚያሳየው ከሆነ የመምህሩ የቅድመ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር በአንብቦ መረዳት ትምህርት ላይ ለጥናቱ የተመረጡት መምህራን ያደረጉት ተሳትፎ ምን እንደሆነ በመረጃ ተጠናቅሮ የቀረበበት ነው። በቅድመ ንባብ ብልሃቶች ስር ከተጠቀሱት መካከል አንዱ የሆነው የምንባቡን ሃሳብ መገመት የሚለው ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሠንጠረዥ 4.1 ተ.ቁ 1.1 ስር የተጠቀሰው ተማሪዎች የምንባቡን ርዕስ ተመልክተው ምንባቡ ስለምን ሊያስገነዝብ እንደሚችል ቀድመው እንዲገምቱ ማድረግ የሚል ሲሆን ይህንንም ተግባር መፈጸም የቻሉት መምህራን በአማካይ ከፍተኛ (8.4%)፣ መካከለኛ (15.6%)፣ ዝቅተኛ (40.7%) እና በጭራሽ (35.3%) የሚሉት ተግባራዊ እንዳደረጉት የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ከዚህም መረጃ መረዳትና ማወቅ የሚቻለው ከፍተኛውን (40.7%) በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ እንዳደረጉት ነው። ይህንን ብልሃት ከመተግበር አንጻር ከጥናቱ ተሳታፊዎች ውስጥ ሶስቱ መምህራን ቅድመ ንባብ ብልሃትን በዝቅተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ ያደረጉ ሲሆን በአንጻሩ ከሌሎች የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል መምህር 5 በተሻለ መልኩ ብልሃቱን ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም አጠቃላይ ብልሃቱን ከመተግበር አንጻር በአማካይ ሲሰላ ከፍተኛ (48%) እና መካከለኛ (52%) ነው።

ተማሪዎች ሠንጠረዡንና ሌሎች ሁኔታዎችን ተመልክተው የምንባቡን ጭብጥ/ይዘት እንዲገምቱ ማድረግን በተመለከተ ከቀረበው ብልሃት አንጻር ሲታይ ደግሞ ምልከታ በተደረገባቸው ሁሉም ክፍለጊዜያት ውስጥ ብልሃቱን በተግባር ላይ ሊውል የቻለው በአማካይ ሲሰላ ከፍተኛ (4.7%)፣ መካከለኛ (9.2%)፣ ዝቅተኛ (51.8%) እና በጭራሽ (34.3%) መሆኑን ከጥናቱ ማወቅ ተችሏል። በአጠቃላይ ከዚህ መረጃ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው መምህራኑ ተማሪዎች ሠንጠረዡንና ሌሎች ሁኔታዎችን ተመልክተው የምንባቡን ጭብጥ/ይዘት እንዲገምቱ በማድረግ በኩል ያለውን ተሳትፎ ስናየው በዝቅተኛ ደረጃ አብዛኞቹ መምህራን ተግባራዊ እንዳደረጉት ማወቅ ይቻላል። ሌላው ብልሃት ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ተማሪዎች ቢያንስ በመጽሃፉ ውስጥ የቀረበውን ሠንጠረዥን ሌሎች ሁኔታዎች ተመልክተው ምንባቡ ምን ይዘት ሊያስተላልፍ እንደሚችል እንዲገምቱ ማድረግ የሚል ሲሆን ይህንንም ብልሃት ተፈጻሚ ከማድረግ አንጻር ከመምህር አብዛኛዎቹ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ ሲያደርጉ ተስተውሏል።

እንዲሁም ከመገመት ብልሃት አንጻር በቅድመ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች የገመቱት ትክክል መሆንና አለመሆኑን በማንበብ ጊዜ እንዲያረጋግጡ በማስረዳት በኩል ያለውን ተሳትፎ

ስንመለከት ሁሉም መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ከጥናቱ መረጃ በመነሳት ማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሰንጠረዥ 4.1 የቀረበው መረጃ እንሚያመለክተው ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ቀድመው የመገመት ብልሃትን ተግብራዊ ማድረጋቸውን፣ የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስ ምንባቡን በተነሳሽነት እንዲያነቡና በማንበብ ጊዜ ምን መተግበር እንዳለባቸው እንዲረዱት ከማድረግ አኳያ ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት መምህራን የሰሩት ስራ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ከመረጃው ውጤት በመነሳት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ተመሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቀደመ(ዳራዊ) እውቀታቸውንና ልምዳቸውን ተጠቅመው ምንባቡን እና በአንብቦ መረዳት ትምህርት ላይ የመማር ማስተማሩ ስራ መጀመር ዋነኛው ተግባር ነው፡፡ በሠንጠረዥ 4.1 በተራ ቁጥር 2 ስር ሶስት ተግባራት የተጠቀሱ ሲሆን ቀዳሚው ተግባር ተማሪዎች ንኡሳን ይዘቱን ከቀረበው ምንባብ ላይ ተነስተው ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ማድረግን የተመለከተ ሲሆን ሁሉም ስድስቱም መምህራን በምልከታ በታዩባቸው ክፍለ ጊዚያት ውስጥ ብልሃቱን ተግባራዊ ለማድረግ የቻሉት በአማካይ በከፍተኛ (6.3%)፣ መካከለኛ (11.4%)፣ ዝቅተኛ (58.4%) እና በጭራሽ (23.9%) መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ መረጃ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው ብልሃቱን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር አብዛኛዎቹ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ትግባራዊ ማድረጋቸውን ነው፡፡

እንዲሁም በብልሃትነት ከተተቀሱት ውስጥ መምህራኑ በርዕሱና በይዘቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ተማሪዎችን እንዲገልጹ መጠየቅና የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ የሚል ሲሆን ተሳታፊ መምህራን በምልከታ በታዩባቸው ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ተፈጻሚ ከማድረግ አንጻር ሁሉም መምህራን በተወሰነ መልኩ ሲተገብሩት ለማየት ተችሏል፡፡

የቀደመ እውቀትን ለመቀስቀስ ከሚረዱ ተግባራት መካከል መምህራኑ በአንጻራዊነት በተሻለ መልኩ ተግባራዊ ያደረጉ ሲሆን ይህን ብልሃት ለመተግበርም ያስችላቸው ዘንድ ለመጠቀም ከሞከሩት ውስጥ ተዛምዶ ያላቸውን ቃላት፣ አባባሎችና ጽንሰሀሳቦች ከሚነበበው ጽሁፍ ጋር ያላቸውን ቁርኝነት ምን እንደሆነ መጠየቅ የሚሉት ሲሆኑ እነዚህን ተጠቅሞ በማስተማና የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስ በኩል ተግባራዊ ያደረጉት መጠነኛ ሲሆን የህንንም በአማካይ ሲታይ ከፍተኛው (12.7%)፣ መካከለኛው (23.2%)፣ ዝቅተኛው (46.5%) እና በጭራሽ (17.6%) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ጥቂት የሆኑት የጥናቱ ተሳታፊዎች ብልሃቱን ምንም ባይተገብሩትም አብዛኞቹ መምህራን ማለትም ከግማሽ

በላይ የሚሆኑት  በጥሩ ሁኔታ መተግበራቸውን እና በስራ ላይ ማዋላቸውን ነው፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ብልሃቱን ከመተግበር አንጻር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ነው፡፡

በሰንጠረዥ 4.1 በተራ ቁጥር 3 የተገለጸው ሌላው ብልሃት ምስል መፍጠር የሚል  ሲሆን ይህም በቅድመ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች ንኡስ ይዘቱን፣ ሰንጠረዥና  ሌሎች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ምንባብ ይዘት በአእምሯቸው በማሰናሰል ምስል መፍጠር እንዲችሉ በማገዝና በመርዳት ተማሪዎቹ አጠቃላይ ትኩረታቸውንና ሃሳባቸውን በሚያነቡት ጽሁፍ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ እንደሚረዳቸው ቢታወቅም ይህን ብልሃት ተግባራዊ ያደረጉት መምህራን ግን በመካከለኛ (24.4%)፣ በዝቅተኛ (42.4%) እና በጭራሽ (33.2%) ደረጃ ተፈጻሚ እንዳደረጉት የመረጃው ውጤት ያሳያል፡፡ ሲጠቃለል ይህን ብልሃት ከመተግበር አንጻር መምህራኑ በዝቅተኛ ደረጃ መተግበራቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሌላውን ብልሃት ስንመለከት ደግሞ የመምህሩ ሞዴል መሆን፣ማበረታታት፣ ድጋፍማድረግ፣ ግብረ መልስና ማጠቃለያ መስጠት በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰ ሲሆን  በስሩ ዝርዝር የሆኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ተጠቅሰዋል፡፡ ከተጠቀሱት ውስጥ ቀዳሚው ብልሃት ውጤታማ ብልሃቶችን ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሞዴል መሆን የሚል ሲሆን ይህንን ብልሃት በክፍል ውስጥ መምህራኑ በምልከታ ጊዜ በታዩባቸው ክፍለ ጊዜያት ተግባራዊ ያደረጉት ከፍተኛው (6.9%)፣ መካከለኛው (19.3%)፣ ዝቅተኛው (27.7%) እና በጭራሽ (46.1%) እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ሲጠቃለል ከዚህ መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ከላይ የተጠቀሰውን ብልሃት በመጠነኛ መንገድ መምህራኑ ተግባራዊ እንዳደረጉት ነው፡፡

ለላው ብልሃት ደግሞ መምህራኑ በተማሪዎች ላይ አስፈላጊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ የሚል ሲሆን ይህንንም ብልሃት መምህራኑ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር በአማካይ ብልሃቱን የተገበሩት ከፍተኛ (11.4%)፣ መካከለኛ (38.2%)፣ ዝቅተኛ (29.4%) ሲሆን በጭራሽ ተግባራዊ ያላደረጉት ደግሞ (21%) መሆኑን ከመረጃው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ትምህርት ጊዜ ተካቶ የሚገኘው ብልሃት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉትን ተማሪዎች በማበረታታት የሚል ሲሆን ይህንንም ብልሃት ተፈጻሚ ለማድረግ ሲባል ሞራል ቀስቃሽ የሆኑትን በጣም ጥሩ፣ ጎበዝ፣ ጥሩ በማለት ተማሪዎችን ማነሳሳትና ማበረታታት ከመምህሩ የሚጠበቅ ተግባር ቢሆንም ይህንን ተግባር በመማር ማስተማር ላይ የተገበሩት በአማካይ ሲገለጽ ከፍተኛ (7.5%)፣ መካከለኛ (34.3%)፣ ዝቅተኛ (39.5%) እና በጭራሽ (18.7%) መሆኑን መረጃው የሳያል፡፡ ከዚህም ውጤት መረዳት እንደሚቻለው መምህራኑ

ይህን ብልሃት ከመተግበር አንጻር ማለትም ተማሪዎችን በማበረታታት በኩል የተሻለ ቢሆንም በረልሃቱን በጭራሽ ተግባራዊ ያላደረጉትን ስናይ ደግሞ ውስን መሆኑንና ፐርሰንቱም (18.7%) እንደሆነ ነው፡፡ነገር ግን ካሉት ደረጃዎች ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው በዝቅተኛ ደረጃ ያለው ሲሆን የተገበሩት መምህራንም በአማካይ (39.5%) ሆኖ ይገኛል፡፡

በመጨረሻም በቅድመ ንባብ ብልሃቶች ስር ከተጠቀሱት ውስጥ አስፈላጊ የሆነ ማስተካከያና ግብረ መልስ መስጠት የሚል ሲሆን ይህን ብልሃት ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ሲገመገም ከምልከታው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ከሆነ መምህራኑ የተገበሩት ከፍተኛ (9.8%)፣ መካከለኛ (45.3%)፣ ዝቅተኛ (20.2%) ሲሆን (26.7%) ደግሞ በጭራሽ ሳይተገብሩት ቀርተዋል፡፡ ከዚህም መረጃ መረዳት እና መገንዘብ የሚቻለው ደረጃቸው ቢለያይም አብዛኞቹ መምህራን ተግባሩን ተፈጻሚ ማድረጋቸውን ነው፡፡ ይሁንና ውስን የሆኑት መምህራን ግብረ መልስ ከመስጠት አንጻር ውስንነት መኖሩን ከመረጃው ለመረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በቅድመ ንባብ ጊዜ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን አብዛኞቹ ስለሚነበበው ምንባብ ተማሪዎች የጋራ ግንዛቤ ይዘው እንዲያነቡና ምንባቡን ከማንባባችው በፊት ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው የማስገንዘብ ውስንነት፣የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ፣ ስለብልሃቶቹ አተገባበር የግንዛቤ / የእውቀት ውስንነት እና የተገነዘቡትንም ምን ያህል ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ከማድረግ አንጻር አርአያ የመሆን ውስንነት ያለባቸው መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ውስን የሆኑት መምህራን አብዛኛውን ቅድመ ንባብ ተግባራትን ሳይተገብሩ በማለፍ በቀጥታ ምንባቡ እንዲነበብ ሲያደርጉ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም እነዚሁ መምህራን አልፎ አልፎ ምንባቡ ከመነበቡ በፊት የተገበሯቸው ተግባራትም ቢሆኑ ለቅድመ ምንባብ ተግባራት የማይሆኑና በብልሃትነት የማይጠቀሱ ተለምዷዊ የሆኑ ተግባራትን ሲያከናውኑ በምልከታ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡ ለአብነት ያህል ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የእለቱን ምንባብ ርዕስ በመናገር በቀጥታ ምንባቡን እንዲያነቡ ማድረግና በለፈው ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የተሰሩትን ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አውዳዊና ፍቺ መስጠት የሚሉትንና መሰል ተግባራትን ተማሪዎችን ሲተይቁና ተማሪዎቹም ለመመለስ ሲሞክሩ በምልከታው ጊዜ ለመረዳት ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ 4.1.1.2 የንባብ ጊዜ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን አንጻር ሲተነተን

| ተ.ቁ | የንባብ ጊዜ ብልሃት | የአተገባበር ሁኔታ አማካይ በመቶኛ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጭራሽ |
| 1 | መረዳትን መከታተል | | | | |
| 1.1 | ማንበባቸውን እየተከታተሉ ቅድመ ግምታቸው ትክክል መሆን አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ማድረግ | - | 17.6% | 82.4% | - |
| 1.2 | ተማሪዎች የምንባቡን ቀሪ ክፍል በማንበብ የግምታቸውን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ ማድረግ | 10.2% | 29.7% | 60.1% | - |
| 1.3 | ንባባቸውን ለተወሰነ ጊዜ አቁመው ወደፊት ምን ሊከሰት እንደሚችል መጠየቅ | - | 24.7% | 75.3% | - |
| 1.4 | መገንዘባቸውን እንዲከታተሉ የሚያስችሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ | - | 20% | 80% | - |
| 2 | ማስታወሻ መያዝ | | | | |
| 2.1 | በሚያነቡበት ጊዜ ግልጽ ያልሆነላቸውን ሃሳብ በማስታወሻ መልክ እንዲይዙ ማስረዳት | - | 10% | 90% | - |
| 3 | የምንባቡን ዋና ሀሳብ መለየት | | | | |
| 3.1 | የንባቡን ዋና መልእክት/ሃሳብ እንዲገነዘቡና እንዲረዱ ማገዝ | - | 33.3% | 66.7% | - |
| 4 | የመምህሩ ሞዴል መሆን፣ማበረታታት፣ ድጋፍ ማድረግ፣ ግብረ መልስና ማጠቃለያ መስጠት | | | | |
| 4.1 | ውጤታማ ብልሃቶችን ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሞዴል መሆን | - | 30% | 70% | - |
| 4.2 | አስፈላጊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | - | 35% | 65% | - |
| 4.3 | ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉትን ተማሪዎች ማበረታታት | - | 29.5% | 79.5% | - |
| 4.4 | አስፈላጊ የሆነ ማስተካከያና ግብረ መልስ መስጠት | - | 15.3% | 84.7% | - |
| 4.5 | ግልጽ ላልሆነላቸው ተማሪዎች ተጨማሪ እገዛ ማድረግ | - | 25.7% | 74.3% | - |

ሠንጠረዥ 4.1.1.2 የንባብ ጊዜ ብልሃቶችን የአተገባበር ሁኔታ የሚየመለክት ሲሆን ይህም የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑትን የመምህራንን መረጃ ባአማካይ ተሰልቶ ለማቅረብ ተችሏል፡፡ በሰንጠረዡ ውስጥ በቀዳሚነት የተጠቀሰው ብልሃት ተማሪዎች በምንባቡ ጊዜ መረዳት አለመረዳታቸውን እንዲከታተሉ የሚያስችል ተግባር በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰ ሲሆን በስሩም ዝርዝር ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ከዝርዝር ተግባራቱ ውስጥ በተራ ቁጥር 1.1 ላይ ያለው ብልሃት ተማሪዎች የምንባቡን ቀሪ ክፍል በማንበብ የግምታቸውን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ ማድረግ የሚል ሲሆን ይህንንም ተግባር መምህራኑ ደረጃው ቢለያይም ለመተግበር ችለዋል፡፡ መምህራኑ ምልከታ በተደረገባቸው በሁሉም ክፍለ ጊዜያት ሁሉም(ስድስቱ) መምህራን የሰሩትን ስራ መጠኑ ቢለያይም ብልሃቱን የተገበሩት ሲሆን በአማካይ ሲቀመጥ ከፍተኛው (17.6%) እና ዝቅተኛው (82.4%) መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የምንባቡን ቀሪ ክፍል በማንበብ የግምታቸውን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ ማድረግ የሚለውን ብለሃት ከመተግበር አንጻር ደግሞ ተግባራዊ ያደረጉት መምህራንን ስንመለከት በአማካይ ከፍተኛው (10.2%)፣ መካከለኛው (29.7%)እና ዝቅተኛው (60.1%) መሆኑን ከምልከታው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጤት መገንዘብ የሚቻለው ዝቅተኛ በሆነ መንገድ የተገበሩት አብዛኞቹ መምህራን እንደሆኑ ነው፡፡

ከመገመት ብልሃት ውስጥ በተራ ቁጥር 1.3 የተገለጸው ሌላው ብልሃት የሆነው ንባባቸውን ለተወሰነ ጊዜ አቁመው ወደፊት ምን ሊከሰት እንደሚችል መጠየቅ የሚል ሲሆን ይህንንም ተግባር በመፈጸም ረገድ ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ሁሉም መምህራን የተገበሩት ሲሆን በአማካይ መካከለኛው (24.7%)፣ ዝቅተኛው (75.3%) ሆኖ ታይቷል፡፡ ከዚህም መረጃ መረዳት የሚቻለው መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁሉም መምህራን ተግባራዊ እንዳደረጉት ነው፡፡

በተ.ቁ 1.4 የተጠቀሰው ሌላው ብልሃት ደግሞ ተማሪዎች መገንዘባቸውን እንዲከታተሉ የሚያስችሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ የሚል ሲሆን ይህንን ብልሃት በተመለከተ ከምልከታው መረጃ ማወቅ እንደሚቻለው በአማካይ መካከለኛው (20%) እና ዝቅተኛው (80%) ደረጃ ተግባራዊ እንደተደረገ ነው፡፡ ከዚህም መረጃ መረዳት የሚቻለው ሁሉም መምህራን መጠኑ የተለያየ ቢሆንም ብልሃቱን በስራ ላይ እንዳዋሉት ወይም ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ነው፡፡

በሠንጠረዥ 4..1.1.2 በተራ ቁጥር 2 የተገለጸው ብልሃት ደግሞ ማስታወሻ መያዝ የሚል ነው፡፡በዚህ ስርም ከተጠቀሱት ውስጥ ተ.ቁ 1 ላይ ያለው ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ግልጽ ያልሆነላቸውን ሃሳብ በማስታወሻ መልክ እንዲይዙ ማስረዳት የሚል ሲሆን ይህንንም ብልሃት ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር በአማካይ መካከለኛው (10%) ፣ ዝቅተኛው (90%) መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ከአፈጻጸም አንጻር ሁሉም መምህራን በመጠን ቢለያይም ተግባራዊ ያደረጉት መሆኑን ከመረጃው መገንዘብ ይቻላል፡፡

የምንባቡን ዋና ሃሳብ መገንዘብ የሚለው ብልሃት በማንበብ ጊዜ ጥቅም ላይ ከሚውሉ ብልሃቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን በስሩም ዝርዝር ተግባራት ይኖሩታል፡፡ ከዝርዝር ተግባራቱም ውስጥ በተራ ቁጥር 3.1 ላይ የተጠቀሰው የንባቡን ዋና መልእክት እንዲገነዘቡና እንዲረዱ ማገዝ የሚል ቀዳሚው ተግባር ሲሆን ይህንንም ተግባር መምህራኑ በክፍል ውስጥ ስለመተግበራቸው ለማረጋገጥ እንደተሞከረው በምልከታው ወቅት የተገኘው መረጃ ሲተነተን መካከለኛው (33.3%)እና ዝቅተኛው (66.7%) መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህም ምልከታ መረጃ መረዳትና ማወቅ የሚቻለው ሁሉም መምህራን መጠኑ ይለያይ እንጂ ብልሃቱን ሲተገብሩት እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

የመምህሩ ሞዴል መሆን፣ማበረታታት፣ ድጋፍ ማድረግ፣ ግብረ መልስና ማጠቃለያ መስጠት የሚለው ብለሃት በንባብ ጊዜ ከሚተገበሩት ብልሃት አብይ ጉዳይ ሲሆን የህም ልክ እንደሌሎቹ ብልሃቶች በስራ ላይ ለማዋል ተሞክሯል፡፡ በዚህ ብልሃት ስር ከተጠቀሱት ዝርዝር ሃሳቦች ውስጥ ውጤታማ ብልሃቶችን ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሞዴል መሆን የሚለው የመጀመሪያው ተግባር ሲሆን ይህንንም ተግባር ሁሉም መምህራን በምልከታ ጊዜ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው ከሆነ በከፍተኛ እና በጭራሽ በሚለው ደረጃ የተከናወነ ምንም ተግባር የሌለ ቢሆንም ነገር ግን በመካከለኛ (30%) እና በዝቅተኛ (70%) ደረጃ ብልሃቱን ተግባራዊ እንዳደረጉትና ተማሪዎችን ከሞላጎደል ሲረዱ እንደነበር ለማየት ተችሏል፡፡

በንባብ ጊዜ የመማር ማስተማሩን ስራ በአግባቡ ማከናወን ይቻል ዘንድ ተማሪዎች ማከናወን ያለባቸውን ተግባራት እያከናወኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ የስፈልጋል፡፡ ለማረጋገጥም ደግሞ መምህሩ ስርአት ባለው መንገድ ተገቢ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ ይኖረበታል፡፡ ምንም እንኳን መምህሩ የእድሜ ደረጃቸው እና የክፍል ደረጃቸው ትንሽ በሆኑ ተማሪዎች ላይ የሚያደርገው ክትትልና ግምገማ ከፍተኛ ቢሆንም ግን የተማሪዎቹ የእድሜ ደረጃና የክፍል ደረጃ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለተማሪዎቹ የሚደረገው ክትትልና ግምገማ በተቃራኒው

ይቀንሳል። ተማሪዎቹ እድሜያቸውና የክፍል ደረጃቸው ሲጨምር አስተሳሰባቸውና የንባብ ክሂላቸውም  አብሮ ስለሚያድግ ነው። ከዚህ እሳቤ ጋር በተያያዘ ተ.ቁ 4.2 ላይ የቀረበውን አስፈላጊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ የሚለውን ብልሃት ከመተግበር አንጻር መምህራኑ በአማካይ የተገበሩት በመካከለኛ ደረጃ (35%)፣ በዝቅተኛ ደረጃ(65%) ነው። ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ የመተግበር ደረጃቸው የተለያየ ይሁን እንጂ ሁሉም መምህራን ሲተገብሩት ታይቷል።

በተጨማሪም በተራ ቁጥር 4.3 ስር የተገለጸውን ብለሃት ስንመለከት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉትን ተማሪዎች ማበረታታት የሚል ሲሆን የህንን ብልሃት በንባብ ጊዜ ተግባራዊ ለማድረግ መምህራኑ ተሳትፎ ለሚያደርጉት ተማሪዎች በተለያየ መንገድ ዋጋ መስጠትና ማበረታታት ይኖርባቸዋል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ተሳትፎ ለሚያደርጉ ተማሪዎች እንዲጨበጨብላቸው በማድረግ የተማሪዎችን ተነሳሽነት መፍጠር ይቻላል። በመሆኑም ይህን ብልሃት መምህራኑ በክፍል ውስጥ በተግባር ላይ ያዋሉትን ስንመለከት  በአማካይ መካከለኛ (29.5%)፣ ዝቅተኛ (79.5%) ሆኖ እናገኘዋለን። ይሁን እንጂ በከፍተኛ  እና በጭራሽ በሚሉት ደረጃዎች የተገበረ መምህር አለመኖሩን የመረጃው ውጤት ያሳያል።

በማንበብ ጊዜ ከተጠቀሱት ብልሃቶች ሌላውን ስናይ ደግሞ ተማሪዎች ለተገበሯቸው ተግባራትና ለተጠየቋቸው ጥያቄዎች አስፈላጊ የሆነ ማስተካከያና ግብረ መልስ መስጠትን የሚመለከት ሲሆን ይህም ብልሃትን በተ.ቁ 4.4 ላይ ይገኛል።  ይህንንም ብልሃት መምህራኑ በክፍል ውስጥ ተፈጻሚ ከማድረግ አንጻር ስንመለከት በአብዛኛው በዝቅተኛ ደረጃ እንደተገበሩት መረጃው ያሳያል። ይህም ማለት ከአፈጻጸም አንጻር አማካዩን ስናይ መካከለኛ (15.3%)፣ ዝቅተኛ (84.7%) ሆኖ እናገኘዋለን። ይሁን እንጂ በከፍተኛ እና በጭራሽ በሚለው ደረጃ  ግን የተገበረ መምህር የሌለ መሆኑን ሰንጠረዡ ላይ ባለው መረጃ መረዳት ይቻላል።

በተ.ቁ 4.5 ላይ የተገለጸውን የመጨረሻውን የንባብ ጊዜ ብልሃትን ስንመለከት ደግሞ ግልጽ ላልሆነላቸው ተማሪዎች መምህራኑ ተጨማሪ እገዛ ማድረግ አለባቸው የሚለውን እናገኛለን። ይህንንም ብልሃት እንደሌሎቹ ብልሃቶች ከሞላ ጎድል ተፈጻሚ ያደረጉት ሲሆን አአማካዩን ስናይ መካከለኛው (25.7%) እና ዝቅተኛው (74.3%) እንደሆነ ከመረጃው ለማወቅ ይቻላል።

በአጠቃላይ የንባብ ጊዜ ብልሃትን አተገባበር በተመለከተ ከተገኘው መረጃ ውጤት አንጻር ስናይ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከቅድመ ንባብ ብልሃቶች አተገባበር በተሻለ መልኩ ሁሉም መምህራን በመካከለኛ እና በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ እንዳደረጉት መረዳት ይቻላል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.1.1.3 የድህረ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን አንጻር ሲተነተን**

| ተ.ቁ | ድህረ ንባብ ብልሃቶች | የአተገባበር ሁኔታ በአማካይ በመቶኛ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጭራሽ |
| 1 | ጥያቄና መልስ | | | | |
| 1.1 | ቀድመው የገመቱት ትክክል እንደሆነና እንዳልሆነ ከነምክንያታቸው እንዲገልጹ መጠየቅ | - | 6% | 94% | - |
| 1.2 | መገንዘባቸውን መረዳት የሚያችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን መጠየቅ | 26.3% | 23.7% | 50% | - |
| 1.3 | በአንድምታና በመመራመር የሚመለሱ ጥያቄዎችን መጠየቅ | - | 55.8% | 44.2% | |
| 2 | በራስ አባባል መግለጽ እና ማጠቃለል | | | | |
| 2.1 | ተማሪዎች ያነበቡትን የምንባብ ዋና ሃሳብ በራሳቸው አባባል እንዲገልጹ ማድረግ | 21.6% | 26.4% | 52% | - |
| 2.2 | አጠቃላይ ያነበቡትን የጽሁፉን ሃሳብ ጨምቀው እንዲገልጹ ማድረግ | - | 35% | 65% | - |
| 3 | ምስል መከሰት /መገንባት | | | | |
| 3.1 | ተማሪዎች ሠንጠረዡን እና ሌሎች ሁኔታዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ምንባብ ምስል በአእምሯቸው መከሰትና መፍጠር እንዲችሉ መርዳት | - | 44.2 | 55.8% | - |
| 4 | የመምህሩ ሞዴል መሆን፣ማበረታታት፣ ድጋፍ ማድረግ፣ ግብረ መልስና ማጠቃለያ መስጠት | | | | |
| 4.1 | ውጤታማ ብልሃቶችን ተማሪዎቹ ተግባራዊ እንዲያደርጉ አርአያ መሆን | - | 37.4% | 62.6% | - |
| 4.2 | አስፈላጊ የሆነ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | 10% | 30.1% | 59.9% | - |
| 4.3 | ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ተማሪዎችን ማበረታታት | 11.5% | 28% | 60.5% | - |
| 4.4 | አስፈላጊ የሆነ ድጋፍ ማድረግ | - | 40.5% | 59.5% | - |
| 4.5 | አስፈላጊ የሆነ ግብረ መልስና የማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት | - | - | 100 | - |

በሠንጠረዥ 4.1.1.3 ላይ የቀረበው የድህረ ንባብ ብልሃቶችን የተመለከተ ሲሆን በክፍል ውስጥ የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት መምህራን ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉት ለማወቅ በምልከታው የተገኘውን መረጃው በአማካይ ተሰልቶ የቀረበበት ነው፡፡

ከድህረ ንባብ በልሃቶች ውስጥ የመጀመሪያውን ብልሃት ተማሪዎች ቀድመው የገመቱት ትክክል እንደሆነና እንዳልሆነ ከነምክንያታቸው እንዲገልጹ የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ብልሃት በሠንጠረዡ ውስጥ በተራ ቁጥር 1.1 ላይ የተካተተ ሲሆን ይህንንም ብልሃት መምህራኑ በምልከታ በታዩበት ክፍለ ጊዜያት እንደተረጋገጠው መምህራኑ በአብዛኛው በዝቅተኛ ደረጃ ለመተግበር ችለዋል፡፡ ይህም ውጤት የተገኘው በምልከታ የተገኘውን መረጃ ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ እንደተገለጸው ብልሃቱን ተግባራዊ ያደረጉት መምህራን በአማካይ መካከለኛ (6%) እና ዝቅተኛ (94%) እንደሆነ ያሳያል፡፡ ከዚህ ውጤት መረዳት የሚቻለው መምህራኑ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ላይ መምህራኑ በክፍል ውስጥ ከመገመት ጋር የተያያዙ ብልሃቶችን መጠቀም እንደቻሉና ብልሃቱንም ተግባራዊ እንዳደረጉት ነው፡፡

በተ.ቁ 1.2 የተጠቀሰው ሌላው የድህረ ንባብ ጊዜ ብልሃት ደግሞ ተማሪዎችን መገንዘባቸውን መረዳት የሚያስችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን መጠየቅ የሚል ሲሆን ይህንን ብልሃት መምህራኑ በምልከታ ጊዜ በተወሰደው መረጃና በተገኘው ውጤት መሰረት በአማካይ ከፍተኛ (26.3%)፣ መካከለኛ (23.7%) እና ዝቅተኛ (50%) በሆነ መልኩ ለመተግበር ችለዋል፡፡ ከዚህም መረጃ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ የህን ብልሃትን በተሻለ ሁኔታ መተግበራቸውንና ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃትን እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንጻር የተሻሉ መሆኑን ነው፡፡

በተ.ቁ 1.3 የተጠቀሰው የድህረ ንባብ ጊዜ ደግሞ በአንድምታና በመመራመር የሚመለሱ ጥያቄዎችን መጠየቅ የሚለው ሲሆን ይህን ብልሃት መምህራኑ በተሻለ ሁኔታ ተግብረውታል ማለት ይቻላል፡፡ መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው ጊዜ ለመተግበር የሞከሩት በአማካይ ሲሰላ መካከለኛ (55.8%) እና ዝቅተኛ (44.2%) ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህም መረጃ ውጤት መረዳት የሚቻለው የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት መምህራን ብልሃቱን ተጠቅመው ተማሪዎችን ለማስተማር መሞከራቸውንና ተማሪዎችም የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ከሚማሩት ትምህርት ጋር በማገናኘት ሃሳቡን ለመረዳትና ለመገንዘብ እንዲሁም ለመገምገም ያደረጉት ጥረት የተሻለ መሆኑን ነው፡፡

በ.ቁ 2 ስር የተጠቀሰው ብልሃት በራስ አባባል መግለጽ እና ማጠቃለል የሚለው ሲሆን ይህም ብልሃት ተማሪዎች የሚያነቡትን የምንባብ ይዘት በተረዱትና በገባቸው ልክ የሚገልጹበትና የማጠቃለያ ሃሳብ የሚሰጡበት ነው፡፡ በዚህ ቢልሃት ስር ንዑሳን ሃሳቦች ያሉ ሲሆን በመጀመሪያ በተ.ቁ 2.1 ላይ የተጠቀሰው ብልሃት እናገኛለን፡፡ ይህም ደግሞ ተማሪዎች የምንባቡን ማእከላዊ ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ እንዲገልጹ ማድረግ የሚል ሲሆን መምህራኑ በመማር ማስተማር ላይ እንዳሉ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ተግባራዊ ያደረጉትን ስናይ በአማካይ ከፍተኛ (21.6%) ፣ መካከለኛ (26.4%) እና ዝቅተኛ (52%) እንደሆነ መረጃው የሚያሳይ ሲሆን ከዚህም አማካይ ማወቅ የሚቻለው መምህራኑ ብልሃቱን በዝቅተኛ ደረጃ እንደፈጸሙት ነው፡፡

እንዲሁም ተማሪዎች አጠቃላይ ያነበቡትን የጽሁፉን ሃሳብ ጨምቀው እንዲገልጹ ማድረግ የሚለው ብልሃት በተራ ቁጥር 2.2 ላይ የተጠቀሰ ይህም ብልሃት ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ ማዕከላዊ ይዘት እንደገልጹ ማድረግን የመለከተ ሲሆን ብልሃቱን የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት መምህራን ስለመተግበራቸው በምልከታ ለማየት ተችሏል፡፡ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለጊዜያትም በአማካይ በመካከለኛ (35%) እና በዝቅተኛ (65%) ደረጃ ብልሃቱን ተግብረውታል፡፡ ከዚህም የምልከታ ውጤት መረዳት የሚቻለው መምህራኑ መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁሉም መምህራን ብልሃቱን የተገበሩት እንደሆነና በአብላጫ ግን በዝቅተኛ ደረጃ መተግበራቸውን ነው፡፡

በተ.ቁ 3 ላይ ምስል መከሰት የሚለው ከድህረ ንባብ ብለሃቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን በስሩም ተማሪዎች ሠንጠረዡን እና ሌሎች ሁኔታዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ምንባብ ምስል በአእምሯቸው መከሰትና መፍጠር  እንዲችሉ መርዳት የሚለው በተ.ቁ 3.1 ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ብልሃት ከጽሁፉ ያገኙትን መረጃዎች መልእክት እንዲያጤኑ ከማስቻሉም በላይ የምንባቡን መልዕክት እንዲያስተውሉት የሚያደርጋቸው ነው፡፡ ይህንንም ብልሃት የጥናቱ ተሳታፊዎች በመማር ማስተማር ላይ ስለመተግበራቸው ለማወቅ ምልከታ የተደረገ ሲሆን የምለከታው ውጤትም የሚያሳየው ብልሃቱን ተግባራዊ ያደረጉት በአማካይ (44.2%) በመካከለኛ እና (55.8%) በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ እንዳደረጉት  ነው፡፡

ሌላው የድህረ ንባብ ተግባር ደግሞ የመምህሩ ሞዴል መሆን፣ማበረታታት፣ድጋፍ ማድረግ፣ ግብረ መልስና ማጠቃለያ መስጠት የሚል ሲሆን በዚህ ተግባር ስር ከተጠቀሱት ብልሃቶች ውስጥ ተራ ቁጥር 4.1 የመጀመሪያው ብልሃት ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መረዳት

አለመረዳታቸውን መገምገም የሚያስችሉ ውጤታማ ብልሃቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ አርአያ መሆን የሚል ሲሆን ይህም ብልሃት መምህራኑ በመማር ማስተማር ላይ ተማሪዎች የምንባቡን  ይዘት እንዲረዱት ለማድረግ ሲሉ የተለያዩ ብልሃቶችን ተጠቅመው ማስተማር እንዳለባቸውና አርአያ መሆን እንዳለባቸቸው የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር  ይህንን ብልሃት ከመተግበር አንጻር መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለ ጊዜያት ተግባራዊ ያደረጉት በአማካይ መካከለኛ (37.4%) እና በዝቅተኛ (62.6%) ሲሆን በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ ያደረገ መምህር የለም፡፡ ይሁን እንጂ መምህራኑ በብዛት በዝቅተኛ ደረጃ ብልሃቱን ተግባራዊ ሲያደርጉት በምልከታው ተስተውሏል፡፡

በተ.ቁ 4.2 ላይ የተገለጸው የድህረ ንባብ ጊዜ ብልሃትን ስናይ ደግሞ አስፈላጊ የሆነ ክትትልና ግምገማ ማድረግ የሚል እናገኛለን፡፡ የዚህ ብልሃት ስፈላጊነት ተማሪዎች በንባብ ጊዜ ክትትል እንደሚያደርጉ እና ሃሳባቸው በትምህረቱ ላይ እንደሆነ ለማወቅ የሚረዳ ነው፡፡ ይህንን ብልሃት ተፈጻሚ ለማድረግ መምህራኑ የተለያ ዘዴን በመጠቀም ይኖርበታል፡፡ ከዘዴዎቹም ውስጥ ተማሪዎችን በተናጥል፣ በጥንድ፣ በቡድን፣  የሚሰሩ ተግባራትን በማመቻቸት፣ ተግባራዊነቱን መከታተልና መገምገም የሚሉት የጠቀሳሉ፡፡ ይህንንም ብልሃት በተመለከተ የመምህራኑ ስለመተግበራቸው የክፍል ውስጥ ምልከታ የተካሄደ ሲሆን በምልከታ የተገኘውም መረጃ የሚያሳየው በአማካይ ከፍተኛ (10%)፣ መካከለኛ (30.1%) እና ዝቅተኛ (59.9%) ተግባራዊ እንዳደረጉት ነው፡፡ ከዚህም መረጃ መረዳት የሚቻለው ይህን ብልሃት አብዛኞቹ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ነው፡፡

በተ.ቁ 4.3 በድህረ ንባብ ጊዜ የተጠቀሰው ብልሃት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ተማሪዎችን ማበረታታት የሚል ሲሆን ይህም ብልሃት በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለሚያደርጉ ተማሪዎች በተለያየ መልኩ ማበረታታትን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህም ብልሃት አንጻር መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለጊዜ የተማሪዎችን ተሳትፎ ያበረታቱት በአማካይ ከፍተኛ(11.5%)፣ መካከለኛ(28%) እና ዝቅተኛ (60.5%) በሆነ ደረጃ ነው፡፡  ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው ሁሉም መምህራን መጠኑ  ይለያይ እንጂ በተለያየ ደረጃ ተግባራዊ ያደረጉት ቢሆንም በዝቅተኛ ደረጃ የተገበሩት ግን ከፍተኛ እንደሆነ ከመረጃው ማወቅ ይቻላል፡፡

እንዲሁም ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነ ድጋፍ ማድረግ የሚለው ብልሃት በተ.ቁ 4.4 ስር የቀረበ ሲሆን ይህም በመማር ማስተማር ወቅት ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ መምህራኑ በተለያየ መንገድ ማለትም ተገቢ ክትትል በማድረግ ምን አይነት ድጋፍ

እንደሚያስፈልጋቸው በማውቅ መደገፍ ያለባቸው መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ መምህራኑም ከዚህ ብልሃት አንጻር ምልከታ በተደረጉባቸው ክፍለጊዜያት ብልሃቱን የተገበሩት በአማካይ መካከለኛ (40.5%) እና ዝቅተኛው(59.5%) ሲሆን በከፍተኛ ደረጃ የተገበረ መምህር አለመኖሩን ከምልከታው የተሰበሰበው መረጃ የሚያሳይ ሲሆን ምንም እንኳን መምህራኑ በመካከለኛ ደረጃ የተገበሩት ያሉ ቢሆንም በብዛት ግን በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ ሲያደርጉት ተስተውሏል፡፡

ከድህረ ንባብ ብልሃቶች ውስጥ የመጨረሻው ብልሃት በተራ ቁጥር 4.5 የቀረበ ሲሆን ይህም ብልሃት ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነ ግብረ መልስና የማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት የሚል ነው፡፡ ይህም ብልሃት ተማሪዎች ለሚጠይቋቸው እና ለሚያነሱት ሃሳብ ምላሽ መስጠት እንዳለባቸውና አጠቃለይ ስለተማሩት ትምህርት የማጠቃለያ ሃሳብ መምህራኑ መስጠት ያለባቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህም ሃሳብ በመነሳት መምህራኑ በክፍል ውስጥ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለጊዜያት ተግባራዊ ያደረጉት በአማካይ ሲታይ ዝቅተኛው (100%) ሆኖ የታያል፡፡ ይህም ማለት ሁሉም መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ አድርገውታል ማለት ነው፡፡

በጥቅሉ የድህረ ንባብ ብልሃቶች አፈጻጸም ሲታይ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከቅድመ ንባብ ብልሃቶችና ከንባብ ጊዜ ብልሃቶች በተሻለ መልኩ የድህረ ንባብ ብልሃቶችን ተግብረውታል ለማለት ያስደፍራል፡፡ ስለመተግበራቸው የምለከታውን መረጃ ተመርኩዘን የድህረ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል መረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ሰንጠረዦች ውጤት እንደሚያሳየው የሁሉም ብልሃቶች ውጤት ሲጨመቅ ሁሉም መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ብልሃቶቹን ተግባራዊ እንዳደረጉት ከምልከታ ውጤት ለማየት ተችሏል፡፡

## 4.2 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግንዛቤ

በጥናቱ እንዲመለስ የታሰበው የጥናቱ ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል? የሚል ሲሆን ይህን ጥያቄ ለመመለስ ያስችላሉ የተባሉትን ጥያቄዎች ተዘጋጅቷል፡፡ ጥያቄዎቹም በአንብቦ መረዳት ትምህርቱ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ሲከናወን ተደረገው ምልከታና በተገኘው መረጃ መሰረት ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት

ተችሏል፡፡ እንዲሁም የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ስለመተግበራቸው ለማወቅ የጽሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁም ሲዘጋጅ መምህራኑ በነጻነት ሃሳባቸውን እንዲገልጹ በሚል በዳሽ ሙላ መልክ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡ ይህም ጽሁፍ መጠይቅ የተዘጋጀበት ዋናው ዓላማ በምልከታ የተገኘው መረጃ ትክክል ስለመሆኑ ለማረጋገጥና የነጠረ መረጃ ለማግኘት ስለተፈለገ ነው፡፡ የሆነው ሆኖ የተዘጋጀውን የጽሁፍ መጠይቅ ለተሳታፊ መምህራን በታቀደው ዕቅድ መሰረት መጠይቁ እንዲደርሳቸውና ሞልተው እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡ ሞልተው የመለሱትን መጠይቅ አንድባንድ ለመፈተሽና ለማየት ተችሏል፡፡ ከጽኁፍ መጠይቁ በፊት በምልከታ የተገኘው መረጃ ሲገመገም ሁሉም መምህራን በምልከታ ቅጹ የቀረቡትን ተግባራት በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ የጽኁፍ መጠይቁን ተግባራት አስመልክቶ የተሰበሰበውን መረጃ በምልከታው ከተገኘውን መረጃ አንጻር በማዛመድ ወይም መሰረት በማድረግ ትንተና ለመስጠት ተችሏል፡፡

## 4.2.1 የቅድመ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግንዛቤ

በሰንጠረዥ 4.1 የምልከታው መረጃ የሚያመለክተው የቅድመ ንባብ ብልሃቶችን ተማሪዎች ርዕሱን አይተው ምንባቡ ስለምን ሊያስረዳ እንደሚችል እንዲገምቱ ማድረግን በተመለከተ ሲሆን አብዛኞቹ መምህራን ተግባሩን መጠኑ ይለያይ እንጂ በመካከለኛና በዝቅተኛ ደረጃ አከናውነውታል፡፡ በምልከታው እንደታየው መምህራኑ በእለቱ የሚነበበውን ምንባብ ርዕስ አብዛኞቹ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከጻፉ በኋላ ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተው የምንባቡን ይዘት እንዲገምቱ ሲያደርጉ ለማየት ተችሏል፡፡ ይህም ተግባር ስለመገመት ብልሃት አተገባበር መምህራኑ በአብዛኛው መጠነኛ ግንዛቤ እንዳላቸው ከመረጃው ማወቅ ተችሏል፡፡ በምልከታ የተገኘውም ይህ ተግባር በጽሁፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን የጽሁፍ መጠይቁ መረጃ ያመለክታል፡፡

ርዕሱን አይተው እንዲገምቱ ማድረግ በሚል የተጠቀሰውን ብልሃት የጥናቱ ተሳተፊዎች ለምን ተግባር ላይ አዋላችሁት ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ ‹‹ተማሪዎች ርዕሱን አይተው ምንባቡ ከማንበባቸው በፊት የምንባቡ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱና ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ከምንባቡ ያገኙትን መልእክት ከግምታቸው ጋር እንዲያመሳክሩ እንዲሁም የምንባቡን ምልክት በትክክል እንዲረዱት ለማድረግ ነው›› ሲሉ መልሰዋል፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎች ከቀረበው ርዕስ ተነስተው የተረዱትን ሃሳብ እንዲገልጹ በማሳተፍ በኩል መምህራኑ በምልከታው በታዩባቸው ክፍለ ጊዜያት ሁሉም መምህራን መጠኑ ይለያይ እንጂ ስለብልሃቱ

ግንዛቤ እንዳለቸው መረጃው ያሳያል፡፡ እንዲሁም ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ተማሪዎች ርእሱን አይተው እንዲገልጹ ያደረጉት ለምን ይሆን? የሚል ጥያቄ በተመሳሳይ በጽሁፍ መጠይቅ እንዲመልሱ ለመምህራኑ የቀረበላቸው ሲሆን የሰጡት ምላሽም የተማሪዎችን የቀደመ እውቀታቸውን ለመለካት እና የመገመት እውቀታቸውን ለመረዳት ነው ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ ከመምህራኑ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው ይህን ብልሃት በመማር ማስተማር ስራ ላይ የተገበሩት ስለብልሃቱ እውቀቱ ያላቸው መሆኑንና ጠቀሜታውንም ጭምር የተገነዘቡ መሆኑን ነው፡፡

በዚህ ሠንጠረዥ ተማሪዎች በርዕሱ፣በንዑሳን ርዕስና በሰንጠረዡ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲገልጹ በመጠየቅ በኩል የምልከታው መረጃ እንደሚያመለክተው ሁሉም መምህራን ሲያስተምሩ በታዩባቸው ክፍለ ጊዜያት መጠኑ ይለያይ እንጂ ስለብልሃቱ ግንዛቤ እንዳላቸው መረጃው ይጠቁማል፡፡ በጠቃላይ መምህራኑ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ርዕሱን፣ ንዑሳን ርዕሶቹንና ሠንጠረዡን ተጠቅመው የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስ ከሚነበበው ምንባብ ጋር በማዋሃድ እንዲያስተምሩት በማድረግ በኩል የጥናቱ ተሳታፊዎች ከሞላ ጎደል ግንዛቤው ያለቸው መሆኑን ከመረጃው ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡

ሲጠቃለል መምህራኑ በቅደመ ንባብ ጊዜ ከሁሉም በተሻለ የተገበሩት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት በመቀስቀስ የሚለውን ተግባር ሲሆን ይህንንም ብልሃት ለመተግብረ የተጠቀሙት ዘዴ ከሚነበበው ጽሁፍ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ጽንሰ ሀሳቦች፣ አባባሎችና ቃላት በመጠየቅና ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ ነው፡፡ በሰንጠረዥ 4.1 የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው የሁሉም መምህራን አተገባበር በአማካይ ከፍተኛ (12.7%)፣ መካከለኛ (23.2%) እና ዝቅተኛ (46%) ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ መምህራኑን የአተገባበር ሁኔታ ከመረጃው መረዳት የሚቻለው ከሞላ ጎደል ሁሉም በሚባል ደረጃ ስለብልሃቱ ግንዛቤ እንዳላቸው ነው፡፡ በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃም ከዚሁ ሃሳብ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡

## 4.2.2 የንባብ ጊዜ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግንዛቤ

በመማር ማስተማር ጊዜ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የንባብ ጊዜ ብልሃቶችን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የንባብ ጊዜ ብልሃቶች በክፍል ውስጥ ተፈጻሚ ከማድረግ አንጻር የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት መምህራን ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉት ለመፈተሽ በሚል መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን በምልካታ የተሰበሰበውን መረጃም

እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በሰንጠረዥ 4.2 መጀመሪያ ላይ እንደተገለጸው በቅድመ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች የገመቱት ትክክል መሆን አለመሆኑን ማንበባቸውን እየተከታተሉ እንዲያረጋግጡ በማስረዳት በኩል መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለ ጊዜያት በመካከለኛ በአማካይ (17.6%) እና በዝቅተኛ (82.4%) መተግበራቸውን ከመረጃው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም የትንተናው ውጤት የሚያሳየው ስለመገመት የአንብቦ መረዳት ብልሃት የክፍል ውስጥ አተገባበር መምህራኑ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

እንዲሁም ተማሪዎች ምንባቡን በሚያነቡበት ወቅት ያልገባቸውንና ግልጽ ያልሆነላቸውን ሃሳብ በማስታወሻ መልክ እንዲይዙ ማስረዳት የሚለው ሌላው ብልሃት ሲሆን ይህንንም ብልሃት ከመተግበር አንጻር መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለጊዜያት እውቀቱ ያለቸው መሆኑን ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ተማሪዎች ምንባቡን እያነበቡ እያሉ ምንባቡ ወደፊት ምን መልዕክት ሊያስተላልፍ እንደሚችል እንዲገምቱ ማድረግና የገመቱትም ግምት ትክክለኛ ስለመሆናቸው የምንባቡን ቀሪ ክፍል በማንበብ እንዲያረጋግጡ ከማድረግ አንጻር የተጠቀሰውን ብልሃት መምህራኑ ተግባራዊ ስለማድረጋቸው በታዩባቸው ክፍለጊዜያት መለወቅ ተችሏል፡፡ መረጃውም እንደሚያሳየው ከሆነ በአማካይ ከፍተኛ (10.2%)፣ መካከለኛ (29.7%) እና ዝቅተኛ (60.1%) ብልሃቱን ተግባራዊ እንዳደረጉት ነው፡፡ በአጠቃላይ ይህንን ብልሃት ከመተግበር አንጻር መምህራኑ ስለብልሃቱ ከሞላጎደል እውቀቱና ግንዛቤው እንዳላቸው መረጃው ይጠቁማል፡፡

እንዲሁም ተማሪዎች ማንበባቸውን ቆም አድረገው ቀጥሎ ምን ሊፈጠር እንደሚችል እንዲገምቱ የመጠየቅ ተግባር የሚለው ሌላው ብልሃት ሲሆን ብልሃቱንም በክፍል ውስጥ መምህራኑ ሲያስተምሩ ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ለማረጋገጥ ምልከታ የተደረገባቸው ሲሆን በአጠቃላይ ምልከታ በተካሄዱባቸው ጊዜያት ተግባራዊ ያደረጉት በአማካይ መካከለኛ (24.7%) እና ዝቅተኛ (75.3%) እንደሆነ ከመረጃው ውጤት ትንተና ለማየት ተችሏል፡፡ ከዚሁ ምልከታ ውጤት ጋር በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃም ተቀራራቢነት ያለው እንደሆነ ከጽሁፍ መጠይቁ ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ተማሪዎች ምንባቡ በሚያነቡበት ጊዜ በመሃል ማንበባቸውን ቆም አድርገው ለጠየቁት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያደረጉት ለምን ይሆን? የሚል ጥያቄ ለመምህራኑ የቀረበ ሲሆን ለዚህም ጥያቄ የሰጡት ምላሽ “ግምታቸውን ከምንባቡ ጋር እንዲያዘምዱ እና የግምት ችሎታቸውን ማዳበር እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡” የሚል ነው፡፡ ከምላሻቸው መረዳት የሚቻለው ስለዚህ ብልሃት አስፈላጊነት ግንዛቤው ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

በሰንጠረዥ 4.2 የተጠቀሰው ሌላው የማንበብ ጊዜ ብልሃት የመምህሩ ክትትልና ግምገማ የተመለከተ ሲሆን ይህም ብልሃት እንደሌሎቹ ተግባራት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ብልሃት መምህራኑ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ስለማድረጋቸው በምልከታ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ትችሏል፡፡ የምልከታው መረጃም እንደሚያሳየው ከሆነ በአማካይ መካከለኛ (35%) እና በዝቅተኛ (65%) ብልሃቱን ተግባራዊ እንዳደረጉት ነው፡፡ ከዚህ ምልከታ ውጤት መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ስለብልሃቱ ከሞላጎደል ግንዛቤው ያላቸው መሆኑንና መተግበር መቻላቸውን ነው፡፡ እንዲሁም በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘውም መረጃ ከዚሁ ሃሳብ ጋር ተቀራራቢነት ያለው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

መምህራኑን ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ በሚያነቡበት ጊዜ በተማሪዎች መካከል እርስዎ እተዘዋወሩ የሚቃኟቸው ምን መተግበራቸውን ለማየት ነው? የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው ሲሆን ለጥያቄው የሰጡት ግብረ መልስ ‹‹በትክክል እያነበቡ መሆናቸውን ለመከታተል፣ ድምጽ ሳያሰሙ ማንባባቸውን ለማረጋገጥ እና ሌሎች የሚያነቡ ተማሪዎችን በድምጽ እንዳይረብሹ ለመቆጣጠር፣ ምንባቡን ትተው ወሬ እንዳያወሩ ለማድረግ ነው›› ሲሉ መልሰዋል፡፡ ከዚህም ምላሻቸው መረዳት የሚቻለው መምህራኑ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለማሻሻል ያደረጉት ጥረት ጥሩ መሆኑንና ስለብልሃቱ የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ሌላው ተግባርን ስንመለከት የተማሪዎችን ተሳትፎ ማበረታታትና ግብረ መልስ መስጠት የሚል ሲሆን ይህም ብልሃት መምህራኑ ተማሪዎችን በንባብ ጊዜ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት እንዳለባቸውና ለሚጠይቁት ጥያቄም ትክክለኛ ምላሽ መስጠት ያለባቸው መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ ብልሃት አንጻር መምህራኑን በምልከታ ለማወቅ የተቻለው  መምህራኑ ስለዚህ ብልሃት እውቀቱና ግንዛቤው ያላቸው መሆኑንና የአተገባበር ግንዛቤ ደረጃቸው ግን ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ከዚሁ ምልከታ ውጤት ጋር  የጽሁፍ መጠይቁ መረጃም ተዛማጅነት አለው፡፡

መምህራኑ በምንባብ ጊዜ ተሳትፎ ላደረጉ ተማሪዎች ጓድኞቻቸው እንዲያጨበጭቡ ያደረጉት ለምንድነው? የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው ሲሆን ለዚህም ጥያቄ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡት መልስም ‹‹የተሳተፉ ተማሪዎችን ተነሳሽነትን ለመፍጠርና ለማበረታታት እንዲሁም በሌላ ጊዜ በንቃት እንዲሳተፉ ለማነሳሳት ነው›› በማለት መልሰዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረበውን የማንበብ ጊዜ ተግባራትን አስመልክቶ ለቀረቡት ዝርዝር ተግባራት መምህራኑ በትክክለኛው መንገድ ብልሃቶቹን ከመተግበራቸው አንጻር ሲፈተሽ የብልሃቶችን አስፈላጊነት በማስገንዘብ፣ ተግባራቱን እንዲያከናውኑ በማለማመድ፣ በማበረታታ፣ ተገቢ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እረገድ ያላቸው ግንዛቤ ከሞላ ጎደል ጥሩ መሆኑን ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 4.2.3 የድህረ ንባብ ብልሃቶች አተገባበር ግንዛቤ

የድህረ ንባብ ብልሃትን በተመለከተ ያሉትን ዝርዝር ተግባራት የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ መምህራን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉ የሚያሳይ መረጃ በሠንጠረዥ 4.3 ቀርቧል፡፡ በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረበውን ዝርዝር ተግባራት ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግና የጽሁፍ መጠይቁን መረጃ በማዋሃድ መምህራኑ ስለብልሃቶቹ አተገባበር ያላቸውን ግንዛቤ እንደሚከተለው ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

ግምትን ማገናዘብ የሚለው የመጀመሪያው ብልሃት ሲሆን ይህም ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ሆነ በንባብ ጊዜ ስለሚያነቡት ምንባብ መልእክት ቀድመው የገመቱት ግምት እና ምንባቡን አንብበው ሲጨርሱ ያገኙት መልእክት ከግምታቸው ጋር ትክክል እንደነበረና እንዳልነበረ እንዲገልጹ ከማድረግ አንጻር ሲፈተሽ ይህን ተግባር ስለመተግበራቸው ለማወቅ እንደተሞከረው መምህራኑ በምልከታ በታዩባቸው ክፍለጊዜያት ሁላቸውም ከሞላጎደል ሲተገብሩት ታይተዋል፡፡ በቀደሙት የንባብ ደረጃዎችም እንደተገለጸው መምህራኑ ከመገመት ብልሃት ጋር ለሚገናኙ ተግባራት በመጠኑም ቢሆን ግንዛቤው እንዳላቸው ከመረጃው ለማውቅ ተችሏል፡፡

እንዲሁም ተማሪዎቸ እንዲያነቡት የተደረገውን ምንባብ መልእክት ካላቸው ዳራዊ እውቀታቸው ጋር በማመሳከር የምንባቡን ጭብጥ ምን ያህል እንደተገነዘቡት መገምገም የሚያስችል ጥያቄዎችን ስለመጠየቃቸው ለማረጋገጥ እንደተሞከረው መምህራኑ በአማካይ ተግባራዊ ያደረጉት መካከለኛ (55.8%) እና ዝቅተኛ (44.2%) ሲሆን ከእነዚህም መካከል አብዛኛው ተግባራዊ ያደረጉት በመካከለኛ ደረጃ እንደሆነ ከመረጃው ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መምህራኑን ተማሪዎች ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ በሚደረግበት ጊዜ ተዛማጅ የሆኑ ጥያቄዎችን የሚጠይቋቸው ለምን ይሆን? ተብለው የተጠየቁ ሲሆን ለተጠየቁት ጥያቄም የሰጡት ግብረ መልስ ‹‹የምንባቡን መልዕክት ምን ያህል

እንደተገነዘቡት ለማወቅ እንዲሁም የተሳሳቱ ካሉም ምንባቡን እንደገና አንብበው እንዲረዱት ለማድረግ ነው›› ሲሉ መልሰዋል፡፡ በማለት ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያደረጉት ለምንድነው? ተብለው የተጠየቁ ሲሆን ለዚህም ጥያቄ የሰጡት ግብረመልስ ‹‹የምንባቡን ይዘት(መልዕክት) ምን ያህል እንደተረዱት ለመገምገም ነው›› በማለት መልሰዋል፡፡

በአጠቃላይ በራስ አባባል መግለጽና ማጠቃለል የሚለውን ብልሃት መምህራኑ ከላይ ከቀረበው ብልሃት ጋር ተቀራራቢነት ባለው መልኩ የተገበሩት ሲሆን ይህም በአማካይ ከፍተኛ (26.3%)፣ መካከለኛ (23.7%) እና ዝቅተኛ (50%) በሆነ ደረጃ እንደተገበሩት የምልከታው ውጤት ያሳያል፡፡

ሌላው ከድህረ ንባብ ብልሃት ውስጥ የሚጠቀሰው ደግሞ ተማሪዎች ሰንጠረዦችንና ሌሎች ሁኔታዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ምንባብ ምስል በአዕምሯቸው መከሰትና መፍጠር እንዲችሉ መርዳት የሚል ሲሆን ይህንን ብለሃት መምህራኑ ስለመተግበራቸው በምልከታ ጊዜ ለማየት እንደተቻለው በአማካይ መካከለኛ (44.2) እና ዝቅተኛ (55.8) በሆነ መልኩ ብልሃቱን ተግብረውታል፡፡ ከዚህም መረጃ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ስለብልሃቱ ከሞላጎደል እውቀቱ ቢኖራቸውም አተገባበራቸው ግን በዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ ነው፡፡

ከሁሉም በተሻለ መልኩ መምህራኑ በድህረ ንባብ ጊዜ ተግባራዊ ያደረጉት ብልሃት አስፈላጊ በሆነ መልኩ ተማሪዎችን መከታተልና ግምገማ ማድረግ ሲሆን ይህንንም ተግባር ከመተግበር አንጻር መምህራኑ የተገበሩት በአማካይ ከፍተኛ (26.3%)፣ መካከለኛ (23.7%) እና ዝቅተኛ (50%) ደረጃ እንደሆነ የመረጃው ውጤት ያመለክታል፡፡ ከዚህም መረጃ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ስለብልሃቱ አተገባበር ከሞላ ጎደል እውቀቱ እንዳላቸው የሚያሳይ ሲሆን በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃም ከዚሁ ሃሳብና መረጃ ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡ ለምሳሌ ያህል ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ ያደረጉት ለምን ይሆን? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ‹‹የንባብ ክሂላቸው ምን ያህል እንደሆነ ለመለካትና ለመገምገም ነው›› መልሰዋል ፡፡

ሌላው ብልሃት ደግሞ ንቁ ተሳትፎ ያደረጉትን ተማሪዎችን ማበረታታት የሚለው ሲሆን ይህንንም ብልሃት በአማካይ መምህራኑ ተግባራዊ ያደረጉት ከፍተኛ (11.5%)፣ መካከለኛ

(28%) እና ዝቅተኛ (60.5%) ሲሆን ከፍተኛውን ደረጃ በዝቅተኛ ሁኔታ መተግበራቸውን የመረጃው ውጤት ያሳያል፡፡ እንዲሁም በጽሁፍ መጠይቁም የተገኘው መረጃም ከዚሁ ውጤት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ነው፡፡ ለምሳሌ ተመሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ ነው የሚሉትን ሲገልጹ እርስዎ ጎበዝ፣ጥሩ ነው እያሉ ያበረታቱት ለምን ይሆን? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ‹‹ድፍረት እንዲኖራቸውና ሞራል ይሆናቸው ዘንድ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ ነው›› በማለት መልሰዋል፡፡

ከላይ የተነሳው ሃሳብ ሲጠቃለል የንባብ ደረጃዎች አተገባበርን በተመለከተ ሰፋ ያለ ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን መምህራኑ ስለድህረ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያለቸው ግንዛቤ በአንጻራዊነት ከቅድመ ንባብና ከንባብ ጊዜ በተሻለ መልኩ እንደተገበሩት ከመረጃው መረዳት ይቻላል፡፡ የንባብ ደረጃዎቹን ከመተግበር አንጻር በቅደም ተከተል ሲቀመጡም ድህረ ንባብ ፣ የንባብ ጊዜ እና ቅድመ ንባብ  በመሆን ከአንድ እስከ ሶስት ያለውን ደረጃ ይይዛሉ፡፡

## 4.3 በአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሰው የመጨረሻው ጥያቄ በሁለቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳይተገብሩ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ወይም ተግዳሮቶች  ምንድን ናቸው? የሚሉ ሲሆን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሊያሰጥ በሚችል መልኩ የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄ ተዘጋጅቷል፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘውንም መረጃ በአይነታዊ የትንተና ዘዴ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተችሏል፡፡

በቀዳሚነት በጽሁፍ ጥያቄነት የቀረበው ጥያቄ የአንብቦ መረዳት ተግባራት የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ ሲሆን በትምህርት ክፍልዎ (በዲፓርትመንትዎ) ከሚገኙ መምህራን ጋር የእርስበርስ የልምድ ልውውጥ ያደርጋሉ? የሚያደርጉ ከሆነ መጠኑን ቢገልጹልኝ? የማያደርጉ ከሆነ ምክኒያቱን ቢገልጹልኝ? የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ከሁሉም መምህራን የተገኘው ምላሽ የልምድ ልውውጥ ከአቻ መምህራን (ከዲፓርትመነት አባላት) ጋር አልፎ አልፎ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡ አክለውም ያገኙትንም ልምድና እውቀት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ እንዲሁም የሚያገኙት ልምድ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ እንዳገዛቸውም ጭምር ተናግረዋል፡፡ ለምሳሌ መምህር 2 ለዚህ ጥያቄ የሰጠው መልስ ‹‹

ልምድ ልውውጥ ማድረጌ የማስተማር አቅሜን እንዳጎለብትና የማስተማር ስነ ዘዴዬ ተሻለ እንዲሆን እረድቶኛል›› በማለት ነው የመለሰው፡፡

በሁለተኛነት የቀረበው ጥያቄ አሁን በምታስተምሩበት የመምህርና የተማሪ መጻህፍት ውስጥ የሚገኙትን የአንብቦ መረዳት ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ስልጠና ወስደዋል? ወስደው ከሆነ ለምን ያህል ጊዜ? ከስልጠናው በቂ ግንዛቤ አግኝተዋል? የሚል ነው፡፡ መምህራኑ የሰጡትም መልስ አብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የ2 ቀን ስልጠና እንዳገኙ እና በተወሰነ መልኩ ግንዛቤ እንደጨበጡና በመጠነኛ ሁኔታ ቢሆን በክፍል ውስጥ እንደሚተገብሩት እነዲሁም ያገኙትን ግንዛቤ በተግባር ላይ በሚያውሉበት ወቅት የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሻለ እንደሚያደርገላቸውም ጭምር ሃሳባቸውን የገለጹ ሲሆን መምህር 3 እና 4 ግን እስካሁን ምንም አይነት ስልጠና እንዳለወሰዱ ገልጸዋል፡፡

በሶስተኛነት የቀረበው በጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ያጋጠመዎትን ችግር ቢገልጹልኝ? የሚል ነው፡፡ መምህራኑ ለዚህ ጥያቄ መጀመሪያ እንደ ችግር ያነሱት ለአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ተማሪዎቹ ተነሳሽነታቸውና ፍላጎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን፣ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ትኩረት አለመስጠት፣ ስለሚማሩት ትምህርት ጥያቄ ከመጠየቅ ይልቅ የግላቸውን ወሬ ማውራትና መረበሽ ወዘተ. ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር በአንድ ክፍል ውሰጥ እስከ 66 የሚደርሱ ተማሪዎች የሚገኙበት ሁኔታ ስላለና ተማሪዎቹን በአግባቡ ለማስተማር አስቸጋሪ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን አክለውም በባህሪያቸው ወጣ ያሉ አንዳንድ ተማሪዎች በመኖራቸው መምህሩ እነሱን አስተካክሎ መማር ማስተማሩን ለማከናወን እንደሚያሰቸግርና የትምህረቱን ጊዜ የሚሻማ እንደሆነ ሃሳባቸውን አስፍረዋል፡፡

እንዲሁም ከጥናቱ ተሳታፊዎች መምህር 5 እንደ አንድ መሰረታዊ ችግር የጠቀሰው ተማሪዎች ሲያነቡ ድምጽ እያወጡ ማንበባቸውና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ያለባቸው በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃትን ለመተግበር አስቸጋሪ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም መምህር 2 ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ የተማሪዎች ቁጥር መብዛቱና ለነሱ የሚዳረስ መጽሃፍ አለመኖሩ ነው ሲሉ መልሰዋል፡፡

ከላይ ለመዳሰስ እንደተሞከረውና የጥናቱን ውጤት ለማጠቃለል ሲሞከር መምህራኑ በቅድመ ንባብ ፣ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ ጊዜ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶን በክፍል ውስጥ በምን

አይነት መልኩ እንተገበሩትና ስለአተገባበሩም ያለቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ያሳየ ነው፡፡ እንዲሁም ብልሃቱን ሲተገብሩ ያጋጠማቸው ችግሮች ምን እንደሆኑ በዝርዝር ያሳየበት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ ጥናት ውጤት መገንዘብ የሚቻለው መምህራኑ የአንብቦ መረዳት ትምህርቱን በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ጊዜ ማለትም የቅድመ ንባብ ተግባራትን ከመተግበር አንጻር ውስንነት እንዳለው ነው፡፡ ይህም መምህራኑ ተማሪዎች ምንባቡን ከመጀመራቸው በፊት ምንባቡን ለምን አላማ እንደሚያነቡና እንዴትስ ማንበብ እንዳለባቸው ግንዛቤ ከመፍጠር አኳያና ሌሎቹንም ብልሃቶች ከመተግበር አረገድ ያላቸው ግንዛቤ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የንባብ ጊዜ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተም መምህራኑ ከቅድመ ንባብ ተግባራት ጊዜ በተሻለ መልኩ ተግባራዊ ያደረጉት ቢሆንም ተማሪዎች በንባብ ጊዜ መተግበር ያለባቸውን ተግባራት እንዲተገብሩ በማድረግ እረገድና መምህራኑም ብልሃቶቹን በመጠቀም ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ተግባራቱ ተገቢውን ልምምድ እንዲያደርጉ በማገዝና ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በኩል የመምህራኑ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተወሰነ መልኩም ቢሆን መምህራኑ ድህረ ንባብ ብልሃቶችን በተሻለ የተገበሩ ሲሆን በተለይ ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የተማሪዎችን የመረዳት ችሎታቸውን ለመገምገም የሚያስችሉ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡና የምንባቡን መልእክትም በራሳቸው አገላለጽ እንዲያብራሩ የሚያደርጉ ብልሃቶችን አዘውተረው መጠቀም እንደቻሉ ጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳይተገብሩ እንቅፋት ወይም የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ ያደረሱ ሁኔታዎች ናቸው ተብለው የተለዩት በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ፣ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት አናሳ መሆንና ተነሳሽነት ማጣት እንዲሁም የመጽሃፍ እጥረት መኖር የሚሉት እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

## 4.4 ጥናቱ የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት ሶስቱን የጥናቱን  ዓላማዎች መሰረት በማድረግ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበርን መመርመር ሲሆን አላማዎቹንም ለመመርመር መረጃዎቹን በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተሰብስበው በአይነታዊ እና በመጠናዊ መተንተኛ  ስልት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በምን አይነት መልኩ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ መመልከት የጥናቱ የመጀመሪያው ዓላማ ሲሆን ከውጤቱም መገንዘብ የሚቻለው መምህራኑ የቅድመ ንባብ ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ያደረጉት በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን የውጤት ትንተናው ያሳያል፡፡ይህም ውጤት Fielding & Pearson (1994) በአንብቦ መረዳት ትምህርት መምህራን ለቅድመ ንባብ ብልሃቶች ተግባራዊነት የሚሰጡት ትኩረትም ሆነ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን ይህም ውጤት ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Hedge (1985) እና Bensoussan (1998) የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በክፍል ውስጥ መምህራን ሲተገብሩ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት በመቀስቀስ ፣ስለምንባቡ አጠቃለይ መልእክት አስቀድመው እንዲገምቱ በማድረግና ምንባቡን በተነሳሽነት እንዲያነቡት በመርዳት እረገድ የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የገለጹ ሲሆን ይህም ጥናታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የትንተናው ውጤት እንደሚያሳየው መምህራን የንባብ ጊዜ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉ ያመላከተ ሲሆን የተገኘው ውጤትም ተማሪዎችን የንባብ ጊዜ ብልሃቶችን በመጠቀም ማንበባቸውን በንቃት እየተከታተሉ የምንባቡን ሀሳብ እንዲረዱት መርዳት የቻሉት መምህራን በመካከለኛና በዝቅተኛ ሁኔታ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ ይህ ውጤት ከማስተዋል (1989) እና ከFielding & Pearson (1994) ዋቢ ካደረጉት Darcin (1978-1979) ጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

በእንዲሁም Othman & Zare (2013) እና Ephrem (2009) ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምንባብ ጨርሰው እንዲያነቡ መምህራን ማድረጋቸው ብቻውን በቂ እንዳልሆነና የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብቃት እንዲጎለብት በማድረግ እረገድ ተማሪዎች በተስማሚ የንባብ ብልሃቶች እየተለማመዱ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማበረታታት፣ መደገፍ እና ክትትል ማድረግ ወሳኝ እንደሆነ በጥናታቸው ከደረሱበት ድምዳሜ ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ከOntary (2003) እና ከDavis (2011) ሀሳብ ጋር የተስማማ ሲሆን ጥናታቸውም የሚያሳው መምህራኑ ተማሪዎች ተስማሚ የንባብ ጊዜ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ማድረግ እና ማስገንዘብ ፣ ተገቢ ክትትል በማድረግ መቼ የትኛው ብልሀት መጠቀም እንዳለባቸው ማሳወቅ እና እገዛ መቼ እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ መርዳት የቻሉት በመካከለኛ እና በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በምን አይነት መልኩ  በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ መፈተሽ የሚል ነው። በትንተናው የተገኘውም ውጤት ከይታያል (2003)  እና ከማረው (1998) ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊ ሲሆን ይህም መምህራኑ በአንጻረዊ ድህረን ንባብ ብልሃቶችን በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረጋቸውን እና ተማሪዎች የዋናውን ሃሳብ በራሳቸው እንዲገልጹ እድል የመስጠት ተግባርን በጥሩ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ጥናቱ ያመላከተ ሲሆን ይህም ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን ሃሳብ ጋር ይስማማል።

ሁለተኛው የጥናቱ አላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጋቸውን ማሳየት ነው። በውጤት ትንተናው እንደተመለከተው መምህራኑ ስለአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ የተሻለ በመሆኑ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ሲያደርጉ ታይተዋል። በመሆኑም የዚህ ጥናት ውጤትም እንደሚያሳየው መምህራኑ ከድህረ ንባብ ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ውስጥ ምንባቡ ከተነበበ በኋላ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ለመገምገም የሚያስችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን በመጠየቅና ተማሪዎች ከምንባቡ የተገነዘቡትን ዋና ሃሳብ በራሳቸው አባባል እንዲገልጹ በመጋበዝ በኩል የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል። በመሆኑም  Nga (2007)  እና ይታያል (2003) የጥናታቸው ውጤት እንደሚያሳየው የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር መካከለኛ እና ዝቅተኛ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት አለው። በተቃራኒው ግን እንግዳ (1992) እና የኔሰው (1990) ባካሄዱት ሙከራዊ ጥናት ያገኙት ውጤት  የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል የመምህራን በብልሃት የተደገፈ ትምህርት የመተግበርና የማስተማር እውቀት ሊኖራቸው ይገባል የሚል ስለሆነ ከዚህ ጥናት ሃሳብ ጋር ብዙም ተደጋጋፊ ሆኖ አይታይም። ይህም መምህራኑ  ውጤታማ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተግባራዊ ማድረግ እና ተማሪዎች እንዲጠቀሙ ማድረግና መርዳት የቻሉት መካከለኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ከመረጃው ማወቅ ተችሏል።

የጥናቱ ሶስተኛው አላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ የሚያሳድሩትን ሁኔታዎችን መለየት ነው። በዚህም መሰረት የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ እንዳይተገብሩ እንቅፋት ከሆኑት  ውስጥ በዋናነት ለአንብቦ መረዳት ትምህርት ትኩረት አለመስጠት፣ የተማሪዎች ፍላጎትና ተነሳሽነት አለመኖር፣ መምህራን ወቅታዊ ስልጠና አለማግኘታቸው ፣

ባንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር መብዛትና በቂ መማሪያ መጸሀፍ አለመኖር መምህራኑ እንዲሁም የእርስበርስ ልምድ ልውውጥ የማድረግ ተነሳሽነት አለመኖር የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ይህም ውጤት በGuthri & etal (2006) ጥናት ከተገለጸው ሀሳብ ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ታይቷል፡፡

እንዲሁም የተማሪዎች የቀደመ እውቀትና የቋንቋ ችሎታ መለያየት የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በክፍል ውስጥ ለመተግበር ሌላው ተጽዕኖ አድራሽ መሆኑ የውጤት ትንተናው አሳይቷል፡፡ ይህም በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያየ ዳራዊ እውቀትና የቋንቋ ችሎታ ስለሚኖራቸው አስቀድሞ መፈተሽ ካልተቻለ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል የሚል ነው፡፡ በጥቅሉ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ ትግበራ ተጽዕኖ ያሳደሩ ተላውጦዎች መኖራቸውን ከጥናቱ ሶስተኛ ዓላማ አንጻር ሲታይ ውጤቱ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እየተጠቀሙ የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን እንዲያጎለብቱ አርአያ መሆን፣ ማስገንዘብ መርዳት የቻሉት በመካከለኛ እና በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ እንዲሁም የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ እንዳይተገበሩ ተጽዕኖ ያሳደሩ ተላውጦች እንዳሉ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ በሚገኙ ሁለት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን የክፍል ውስጥ አተገባበር ለመመርመር አላማ አድርጎ የተካሄደ ነው፡፡ ለዚህ አላማ መሳካትም በጥናቱ እንዲመለሱ የታሰቡት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

በጥናቱ መልስ ያገኙት የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄዎች፡-

4. በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ምን ያህል ተግባራዊ እያደረጉ ነው?
5. በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?
6. በሁለቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን እንዳይተገብሩ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

እነዚህን የምርምሩን መሰረታዊ ጥቄዎች በአግባቡ ለመመለስ፣ ዓላማዎቹንና መላምቶቹን ለመፈተሽ ጥናቱ እንደሚከተለው ተከናውኗል፡፡

በቅድሚያ የጥናቱ ተሳታፊዎች በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ የሚገኙ ሁለት የመንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡ ሲሆን በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ካሉት የክፍል ደረጃዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ 9ኛ ክፍል ተመርጧል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ በ2015 ዓ.ም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተመረጠው ስራ ላይ የዋሉት ምልከታ አና ጽሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ ከነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ ውስጥ ምልከታ እንደዋና መረጃ መሰብሰቢያነት

ሆኖ አገልግሏል፡፡ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመፈተሽ የሚያስችል ቅጽ  የተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህርና የተማሪ መጽሀፍት በማየት የጥናቱ ተሳታፊዎች የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜ እና የድህረ ንባብ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን የክፍል የውስጥ አተገባበር ሁኔታ በመገምገም ነው፡፡ ቅጹ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት ከመዋሉ በፊት የምርምር ልምድ ባላቸው ሰዎችና በጥናቱ አማካሪ ተገምግሞ ከዋናው ጥናት በፊትም በሙከራው ጥናት ተፈትሾ ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ አስተማማኝነቱም ስለታመነበት ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋለው  የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን ይህም በክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ ከተገኘው መረጃ ጋር ለማመሳከርና አዳዲስ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሲባል ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የጽሁፍ መጠይቁ ሲዘጋጅ ምልከታውን መሰረት ያደረገና መምህራኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ለማወቅ የሚያስችሉ 20 የግንዛቤ መመርመሪያ ጥያቄዎች አካቷል፡፡ እንዲሁም መምህራኑ ብልሃቶቹን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንዳያደርጉ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉ ሶስት ጥያቄዎችን በማካተት መረጃው ተሰብስቦ ተተንትኗል፡፡

በአጠቃላይም የጥናቱ ውጤትም የሚሳየው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቅድመ ንባብ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አተገባበር ዝቅተኛ መሆኑን ፣ በንጽጽር የንባብ ጊዜና የድህረንባብ ብልሃቶች አተገባበር የተሻለ መሆኑን ነው፡፡ ይህን ውጤት መነሻ በማድረግም ቀጥሎ የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማዎች ቀርበዋል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄዎችን የተመለሱ ሲሆን አላማዎቹ ተፈትሸው በጥናቱ የተደረሰባቸውን መደምደሚያዎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦችና ጥቆማዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1.ለጥናቱ የተመረጠው የክፍል ደረጃ 9ኛ ክፍል ሲሆን አሁን በማስተማሪያነት እያገለገለ ያለውን የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ላይ ያተኮረ በመሆኑ መምህራኑ ምንባቡን ተማሪዎቹ ከማንበባቸው በፊት የክፍሉን ጸጥታ ሁኔታ ቢመመቻች

2. የተማሪዎቹን የማንበብ ፍላጎትን የሚቀሰቅሱ ነገሮችን መጠቀም ቢቻል

3.መምህራኖች ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ስለጠና ቢሰጣቸው

4.እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርና የመምህራኑ ተነሳሽነት በተመለከተ ወደፊት ቀጣይነት ባለው መንገድ ሰፋ ያለ ጥናት ቢካሄድ የሚል ነው፡፡

# ዋቢ ፅሁፎች


ማረው አለሙ:: (1998)፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ::* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ማስተዋል ውበቱ:: (1989):: "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ

በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ

የተካሄደ ጥናት" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል መሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታታመ)፡፡

ሰርካለም ይገረሙ፡፡ (2010)፡፡ " አእምሮኣዊ እና ልእለአእምሮኣዊ የማንበብ ብልሃቶች አማርኛ ሁለተኛ

ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለቸው አስተዋጽኦ (በሰንዳፋ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (ያልታተመ)::

እሱባለው ወልደገብርኤል:: (2010)፡፡ "የማንበብ ብልሃትን በግልጽ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማጎልበት እና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋጽኦ፣በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ 9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፌት ተማሪዎች ተተኳሪነት"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለ "PhD" ትምህርት መርሀግብር ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (ያልታተመ)::

እንድሪስ አባይ:: (2000)፡፡ "የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መማር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ "በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (ያልታተመ)::

እንግዳ ዘውዴ፡፡ (1992)፡፡ የ"ቶፕዳውን" (Top-down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት፣ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

በረከት ሁሴን:: (2010)፡፡ "በሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞን በሰገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢአፍፌት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ ለተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር "አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኤም.ኤ.ዲግሪ መሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)::

ተክላይ ተእዛዙ:: (2000)፡፡ ''በትግረኛ ቋንቋ ዘፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍልና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ፍተሻ፣በአክሱም ከተማ 1ኛ ደረጃና 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መነሻነት ''በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)::

ዘውዱ መብሬ:: (2008):: "ሚናዋጭ ዘዴ የአማርኛ አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትን ችሎታና የማንበብን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋጽኦ፡-በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት (ያልታተመ)::

የኔሰው ደሴ፡፡ (1990)፡፡ "በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

ይታያል ወርቁ፡፡ (2003)፡፡ "የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሶስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርትቤቶች በስምንተኛ ክፍል ተተኳሪነት" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

Ajidhe,p. (2006). Schema Theory Based Consideration on Pre- reading Activities in ESP Text Book: The Asian EFL jornal teaching articles, Vol.16.

Alderson, C.J. and Urquhart, A.H.(1984). *Reading in Foreign Language*. New York: Longman Inc.

Anderson, N. (1991). *Individual Differences in Strategy use in Second Language Reading and Teasting*. The Modern Language Journal Vol. 7,5N,2 pp 46-72.

Alfassi, M. (2004). *Reading to Learn: Effectes of Combined Strategy Instructionon High School Studentes*. The Journal of Educational Research, 97(4),171-185.

Aloqaili, A.S.(2012). *The Relationship Btween Reading Comprehension and Critical Thinking*: A theoretical study, Journal of King Saund University-Language And Translation. Retrieved from W W W. Scienceedirect.com.

Anderson, N.J. (1999). *" Improving Reading Speed Activities For Classroom*" English Teaching Forum Vol.37,no.2 april.

Bensoussan, M. (1998). *Schema effects in EFL Reading Comprehension*. University of Haifa, Israel. Vol. 21, Issue 3.

Blazer, Christie. (2007). *Reciprocal Teaching*. Information and Research service, Vol. 0609.

Bolck, E. (1986). *The Comprehension Strategies of Second Language Readers.TESOL*. Quarterly,20,463-494.

Chair, S, C. (2002). *Reading for Understanding toward Research and Program in Reading Comprehension.* RAND Reading Study Group: U.S. Department of Education.

Chamot, A. U. (1987). "*The Learning strategies of ESL Studentes*" in Wenden, A. and Rubin, J. (eds.) (1987) *Learner Strategies in Language Learning*. Cambridge: Oxford: Cambridge University Press.

Conley, M.W. (1992). *Content Reading Instruction*: Communication Approach.New york: Mc Graw-Hill.

Cubukcu, F. (2007). *An Investigation of Reading Strategies Employed by Trainee Teachers*. GEMA online Journal of Languate Studies, Vol. 7(2) pp 95-110.

Davis, A. (2011). *Building Comprehension Strategies for the Primary years*. Eleanor Curtain publishing. Levell. Cuite3.

Davies, F. (1995). *Introducing Reading*. Cambridge: Cambridge University Press.

Ellis, R. (1994*). Understanding Second Language Acquisition.* Oxford: Oxford University press..

Ephrem,K.(2009). *Reading Comprehension Instruction for Expositori text in Elementary Education.* Liberty University.

Grellt, F. (1981). *Developing Reading Skills. A Practical Guide to Reading Comprehensive Exercise (1st ed.).*Cambridge: Cambridge University press.

Grellet, N. (1990). *Developing Reading Skills: a practical Guide to Reading Comprehension Exercices.* Cambridge: Cambridge University Press.

Greenwood, J. (1981). *"Compensation and Reading". In Abbott,g.and Wingard,p.(eds) Teaching of English as an International Language*: A practical Guide. Oxford; University Press.

Gray, A. (2008). *Constructivist Teaching And Learning.* Retrieved from http://WWW.sanksschoolboards.ca/old//Reaserch And Development/Instruction/.97-07.

Guthri, T. & etal. (2006). *Influence of Stmulating Taskes on Reading Motivation and Comprehension.* University of Mary Land. Vol.99, no.4.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching*. New york: Longman.

Harmer, J. (2001). *The Practiceof English Language Teaching*. ESSEX: Pearson Education Limited.

Hedge, J. (1985). *Using Readers in Language Teaching*. London: Macmillan Publishers Ltd.

Hoftman, J. Baomann, J. and Afflerbach, P. (2000). *Balancing Principles For Teaching Elementary Reading.* Mahwah, NJ: Erlbaum.

Lubliner, S. (2001). *A Practical Guide to Reciprocal Teaching*. Bothell, WA: Wright Group.

McNamara, D. S. (2007). *Reading Comprehension Strategies: Theories, Interventions, and Technologies, Mahwan, New Jersey*: Lawrence Erlbaum Associates, Inc., Publishers.

Middleton, R. (1989). *Strategies For Teaching Reading*: International Reading Association,22/8.

Moates, L. C. (1999). *Teaching Reading Is Rocket Scince: What Expect Techears of Reading Should know and be able to do.* University of Texas: Houston Health Science Center.

Mokhtari, K. and Reichard, C.A. (2002*). Assessing Students Metacognitive Awarenss of Reading Strategies.* Journal of Educational Psychology: American Psychological Association Inc. 022-0603:DOI:10:1037/0022-0663.94.2.249 Vol 94 no 2 249-259.

Nga, N. (2007). *Teachers Beliefs About Teaching Reading Strategies And Their Classroom Practice: Acase Study of viet ba High School*. Vietnam National University College Of forien Languages. Department of Post Graduate Studies.

O,Malley, J.M.,Chamot, A.U.,Stewner-Manganaves, G, Russo, R.P.And Kopper,L. (1985). *Learning Strategy Applications with Studentes of English as a Scond Language*. TESOL Quarterly:Vol 19(3),pp 557-584.

Othman, M. & Zare, P. (2013). *The Relationship between Reading Comprehension and Reading Strategy use among Malaysian ESL Learners*: International Journal Of Humanities And Social Science. Vol. 3, no.13.

Palincsar, A. and Brown, A.L. (1984). *Reciprocal Teaching of Comprehension-Fostering and Comprehension Monitoring Activities*. Cognition and Instruction,1(2),117-175.

Panmanee, Wanpavee (2009) "Reciprocal teaching procedure And Regular Reading Instruction: Their Effects on Students Reading Development." Thai: prince of Songkla University MA Thesis.

Pearson,Dvid (2009*). Historical Perspectives on Reading Comprehension: The Roots of Reading Comprehension*. In Duffy, Gerald G.& Israel, Susan E. (Eds.) Handbook Of Research on Reading Comprehension. New York: Routledge.

Phakiti, A. (2006). Theoretical And Pedagogieal Issues In ESL/EFL Teaching of Strategic Reading TESOL, N I, pp 19-50.

Pressley, M . (2002). *Metacognitive and Self Reguleted Comprehension in Farstrup A.E. And Samules, S. J. (Eds) what Research has to say about Reading Instructoin (3rd Ed) Network, DE*: International Reading Association. PP 243-260.

Rowell, C. G., & Palmer, B. C. (2007). *Cognitive and Constructivist Strategies for Teaching About Language and for Providing Reading and Writing Instruction*. Forum on Public Policy pp 1-30.

Rubin, J. (1975). *What the "Good Language Learner" Can Teach us*. TESOL Quarterly 9/2 pp 41-51.

Seid Mohammed (2012). *"Effects Of Cooperative Learning on Reading Comprehension Achievement In EFL And Social Skills of Grade 10 Students*." Addis Ababa: Addis Ababa University PHD Thesis.

*Sheng, H.J. (2000). Cognitive Model for Teaching Reading Comprension*. English Teaching Forum, Vol. 38, No. 4, 12-15.

Snow, C. E. (2002*). Reading for Understanding*: Torard a Research and Development Program in Reading Comprehension Santa Monica, CA: RAND.

Snow, C. E., & Sweet, A. P.(2003*). Reading for Comprehension*. In A. P. Sweet and C. E.Snow (Eds), Rethinking Reading Comprehension (pp. 1-11). NY:Guilford press.

Tankersiey, K. (2005). *Literacy strategies for Grades 4-12 Reinforcing the Tredes of Reading*: Association for Supervision and Curriculum Development. Alexandria,Virginia USA.

Ur, P. (1996*). A Course In Lnguage Teaching Practice and Theory*. Great Britain: Cambridge University Press.

Wallace, C. (1992). *Reading Oxford*: Oxford University press.

Wei, Y. (2005*). The Relationship Between Phonological Awareness and Reading Ability of The Students in English and Thai Primary Schools of Thailand. Doctoral Dissertation*. University of Maryland,College Park. College Park:MD.

Williams, E. (1984). *Reading in the Language Classroom*. London: Macmillan Publishing.

.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ. የምልከታ መገምገሚያ ቅጽ

ቀን፡- ………………  የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ፡- ………………

ሰዓት፡- ……………..  የክፍል ደረጃ ፡-……………………

ክፍል፡- ………

በክፍል ውስጥ ትምህርት እየቀሰሙ ያሉ ተማሪዎች ብዛት ወ፡- …. ሴ፡- ……. ድ፡-……

የት/ቤቱ ስም ፡-………………..

ለሚያስተምረው መምህር/ ርት የተሰጠ ኮድ/ መለያ፡-……………

ተመልካች፡- ……………………

የምልከታ ጊዜ ፡- 1ኛ 2ኛ 3ኛ 4ኛ 5ኛ

የመገምገሚያ እርከኖች ፡- ከፍተኛ(4) ፣ መካከለኛ(3) ፣ ዝቅተኛ(2) ፣ በፍጹም(1)

| ተ.ቁ | አንብቦ መረዳት ብልሃቶች | የአተገባበር ሁኔታ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | ቅድመ ንባብ ብልሃቶች | | | | |
| 1. | ተማሪዎች የምንባቡን ርዕስ ተመልክተው ምንባቡ ስለምን ሊያስገነዝብ እንደሚችልቀድመው እንዲገምቱ ማድረግ | | | | |
| 2. | ተማሪዎች ሠንጠረዡንና ሌሎች ሁኔታዎችን ተመልክተው የምንባቡን ጭብጥ/ ይዘት እንዲገምቱ ማድረግ | | | | |
| 3. | ንኡሳን ይዘቱን ከቀረበው ምንባብ ላይ ተነስተው ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ማድረግ | | | | |
| 4. | በርእሱና በንኡሳን ይዘቱ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲያንጸባርቁ ማድረግ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5. | ተዛምዶ ያላቸውን ቃላት፣ አባባሎችና ጽንሰሀሳቦች ከሚነበበው ጽሁፍ ጋር ያላቸውን ቁርኝነት  በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ | | | | |
| 6. | ተማሪዎች ንኡስ ይዘቱን፣ ሰንጠረዥና  ሌሎች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ምንባብ ይዘት በአእምሯቸው ምስል መፍጠር እንዲችሉ ማገዝ | | | | |
| 7. | ውጤታማ ብልሃቶችን ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሞዴል መሆን | | | | |
| 8. | አስፈላጊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | | | | |
| 9. | ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉትን ተማሪዎች ማበረታታት | | | | |
| 10. | አስፈላጊ የሆነ ማስተካከያና ግብረ ግብረ መልስ መስጠት | | | | |
| | **የንባብ ጊዜ ብልሃቶች** | | | | |
| 1. | ማንበባቸውን እየተከታተሉ ቅድመ ግምታቸው ትክክል መሆን አለመሆኑን  እንዲያረጋግጡ ማድረግ | | | | |
| 2. | የምንባቡን ቀሪ ክፍል በማንበብ የግምታቸውን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ ማድረግ | | | | |
| 3. | ንባባቸውን ለተወሰነ ጊዜ አቁመው ወደፊት ምን ሊከሰት እንደሚችል መጠየቅ | | | | |
| 4. | መገንዘባቸውን እንዲከታተሉ የሚያስችሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ | | | | |
| 5. | በሚያነቡበት ጊዜ ግልጽ ያልሆነላቸውን ሃሳብ በማስታወሻ መልክ እንዲይዙ ማስረዳት | | | | |
| 6. | የንባቡን ዋና መልእክት/ሃሳብ እንዲገነዘቡና እንዲረዱ ማገዝ | | | | |
| 7. | ውጤታማ ብልሃቶችን ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሞዴል መሆን | | | | |
| 8. | አስፈላጊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | | | | |
| 9. | ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉትን ተማሪዎች ማበረታታት | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 10. | አስፈላጊ የሆነ ማስተካከያና ግብረ ግብረ መልስ መስጠት | | | | |
| 11. | ግልጽ ላለባቸው ተማሪዎች ተጨማሪ እገዛ ማድረግ | | | | |
| | **ድህረ ንባብ ብልሃቶች** | | | | |
| 1. | ቀድመው የገመቱት ትክክል እንደሆነና እንዳልሆነ ከነምክኒያታቸው እንዲገልጹ መጠየቅ | | | | |
| 2. | መገንዘባቸውን መረዳት የሚያችሉ ምንባብ ተኮር ጥያቄዎችን መጠየቅ | | | | |
| 3. | በአንድምታና በመመራመር የሚመለሱ ጥያቄዎችን መጠየቅ | | | | |
| 4. | ተማሪዎች ያነበቡትን የምንባብ ዋና ሃሳብ በራሳቸው አባባል እንዲገልጹ ማድረግ | | | | |
| 5. | አጠቃላይ ያነበቡትን የጽሁፉን ሃሳብ ጨምቀው እንዲገልጹ ማድረግ | | | | |
| 6. | ተማሪዎች ሠንጠረዡን እና ሌሎች ሁንታዎችን ተጠቅመው ስለሚነበበው ምንባብ ምስል በአእምሯቸው መከሰትናመፍጠር እንዲችሉ መርዳት | | | | |
| 7. | ውጤታማ ብልሃቶችን ተማሪዎቹ ተግባራዊ እንዲያደርጉ አርአያ መሆን | | | | |
| 8. | አስፈላጊ የሆነ ክትትልና ግምገማ ማድረግ | | | | |
| 9. | ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ተማሪዎችን ማበረታታት | | | | |
| 10. | አስፈላጊ የሆነ ድጋፍ ማድረግ | | | | |
| 11. | አስፈላጊ የሆነ ግብረ መልስና የማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት | | | | |

## አባሪ ለ. የጽሁፍ መጠይቅ ቅጽ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ በሚገኙ ሁለት ት/ቤቶች ማለትም በጀንበሮ ከፍተኛ እና በአረቅጥ ከፍተኛ ት/ቤቶች ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

የዚህ ጽሁፍ መጠይቅ ዓላማ ለማከናውነው ጥናት መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም የእርስዎ ትክክለኛ መረጃ መስጠት ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በቅድሚያ ለሚደረገው የጽሁፍ መጠይቅ ፍቃደኛ በመሆንዎ ከልብ እያመሰገንኩ የሚሰጡኝ ማንኛውም መረጃ ለዚህ ጥናት ዓላማ ብቻ የሚውል መሆኑን መግለጽ እወዳለው፡፡

-ስለትብብራችሁ አመሰግናለው፡፡

-ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

**ቅድመንባብ ብልሃቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች**

1. ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ከሚነበበው ምንባብ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጥያቄዎችን የጠየቁት ለምን ይሆን?...................................................( ለመምህር 1 እና 3 የቀረበ ጥያቄ)
2. ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የእለቱን የምንባብ ርእስ አይተው እንዲገምቱ/እንዲገልጹ የደረጉት ለምን ይሆን?.................................................... ........................................................( ለመምህር 6 የቀረበ ጥያቄ)
3. ተማሪዎች ለተጠየቁት ጠያቄ ምላሽ ከሰጡ በኋላ እርስዎ አልፎ አልፎ ምላሽ ሲሰጡ ነበር፡፡ይህን የተገበሩት ለምን ይሆን?.................................................................... ..................................................( ለመምህር 1፣ 3 እና 5 የቀረበ ጥያቄ)
4. ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ባለፈው ክፍለ ጊዜ ካዳመጡት ምንባብ በክለሳ እንዲገልጹ ያደረጉት ለምን ይሆን?.............................................................. .........................................................................( ለመምህር 1 የቀረበ ጥያቄ)
5. ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ተማሪዎች ርዕሱን አይተው እንዲናገሩ ያደረጉት ለምን ይሆን? ከዚህ ተግባር ጋር ሊጨመር የሚችል ተግባር ካለ ቢገልጹልኝ፡፡ .......................................................................................... .................................................( ለመምህር 3 የቀረበ ጥያቄ)

6. ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ባለፈው ክፍለጊዜ በክፍል ውስጥ የተሰሩትን ለቃላት  አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መስጠት ጥያቄዎች  በዛሬው ክፍለጊዜ በክለሳ እንዲሰሩ ያደረጉት ለምን ይሆን ?......................
………………………………………………………………(ለመምህር 4 የቀረበ ጥያቄ)
7. ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስለንኡሳን ርዕሶች ያስተዋሉትን  እንዲገልጹ ያደረጉት ለምን ይሆን?..........................................................................
……………………………………………………....... (ለመምህር 6 የቀረበ ጥያቄ)

## የንባብ ጊዜ ብልሀቶችን የተመለከቱ ጥያቄዎች

1. በማንበብ ጊዜ የተወሰኑ ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ ተራ በተራ ምንባቡን እንዲያነቡ ያደረጉት ለምንድነው?............................................
………………………………………………………… ( ለመምህር 6 የቀረበ ጥያቄ)
2. ምንባቡ በሚነበብበት ጊዜ በምንባቡ መሃል ሲደረሱ ተማሪዎች ማንበባቸውን ገታ አድረገው የምንባቡን ጥያቄ  እንዲመልሱ /እንዲገምቱ ያደረጉት ለምን ይሆን?..........................................................................
……………………………………………… ( ለመምህር 1፣ 5 እና 6 የቀረበ ጥያቄ)
3. በማንበብ ጊዜ ተሳትፎ ላደረጉ ተማሪዎች ጓደኞቻቸው እንዲያጨበጭቡላቸው ያደረጉት ለምን ይሆን ?  ከዚህ  ተግባር ጋር ሊጨመር የሚችል ተግባር አለ ?  ቢገልጹልኝ፡፡
………………………………………………………………………………
………………………………………………………. (ለመምህር 1 የቀረበ ጥያቄ)
4. ተማሪዎች ምንባቡን በለሆሳስ በሚያነቡበት ጊዜ እርስዎ በተማሪዎች መካከል እየተዘዋወሩ የሚቃኟቸው ምን መተግበራቸውን ለማየት ነው?...........................
…………………………………….. ( ለመምህር 1፣2፣3፣ እና 6 የቀረበ ጥያቄ)
5. ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ “አሁን አንተ ማንበብህ ነው?/ማንበብሽ ነው?” የሚሏቸው አንዳንድ ተማሪዎች አሉ፡፡ ይህን የሚሉት ለምን ይሆን ?..........................................................................................
………………………………………… (ለመምህር 3 የቀረበ ጥያቄ)
6. ተማሪዎች ምንባቡን በቡድን በሚያነቡበት ጊዜ እርስዎ በተማሪዎች መካከል እየተዘዋወሩ የሚቃኟቸው ምን መተግበራቸውን ለማየት ነው?................................
……………………………………………….. (ለመምህር 2 እና 4 የቀረበ ጥያቄ)
7. እርስዎ ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የተዋሰኑ ተማሪዎች ተራ በተራ እየወጡ እንዲያነቡ ያደረጉት ለምን ይሆን ? ……………………………………………………
…………………………………………………… (ለመምህር 5 የቀረበ ጥያቄ)

### ድህረ ንባብ ብልሃቶችን የተመለከቱ ጠያቂዎች

1. ተማሪዎች ለጥያቄዎች ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ አልፎ አልፎ እጅ ያላወጡ ተማሪዎችን የጠየቋቸው ለምን ይሆን?.......................................................

   ....................................................................................................

   . (ለመምህር 6 የቀረበ ጥያቄ)
2. ተማሪዎች ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ በሚደረግበት ጊዜ አልፎ አልፎ ተያያዥ የሆኑ ጥያቄዎችን የጠየቋቸው ለምን ይሆን?.......................................

   ............................................................... (ለመምህር 4 የቀረበ ጥያቄ)
3. ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኂላ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች  ምላሽ እንዲሰጡ ያደረጉት ለምን ይሆን?.................................................................................

   ....................................... (ለመምህር 1፣ 2፣ 3 ፣ 4፣ 5፣ 6፣ የቀረበ ጥያቄ)
4. ተማሪዎች ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በቡድን ሰረተው እንዲያንጸባርቁ ካደረጉ በኂላ በተማሪዎችና በርስዎ ለቡድኖቹ ደረጃ እንዲሰጥና እንዲጨበጨብላቸው ያደረጉት ለምንድነው?..................................................................................

   ........................................................ (ለመምህር 1 የቀረበ ጥያቄ)
5. ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ ነው የሚሉትን ሲገልጹ እርሰዎ “ጎበዝ “ “ጥሩ ነው!” ይላሉ፡፡ የህን የተገበሩት ለምን ይሆን? ከዚህ ተግባር ጋር ሊጨመር የሚችል ተግባር አለ? ቢገልጹልኝ:: ……………………………………………………………..

   …………………………………………………………. (ለመምህር 2 የቀረበ ጥያቄ)
6. ተማሪዎች ለጥያቄዎች ምላሽ ከሰጡ በኂላ እርሰዎ አልፎ አልፎ ምላሽና ገለጻ ሲሰጡ ነበር፡፡ ይህን የተገበሩት ለምነድነው? ………………………………………………….

   ……………………………………. (ለመምህር 1፣ 3፣ 4፣ 5፣ እና 6 የቀረበ ጥያቄ)

የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን  የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ያጋጠሟቸውን  ችግሮች አመላካች ጥያቄዎች

1. የአንብቦ መረዳት ተግባራትን የክፍል ውስጥ አተገባበር በተመለከተ በትምህርት ክፍልዎ (በዲፓርትመንትዎ) ከሚገኙ መምህራን ጋር የእርስበርስ የልምድ ልውውጥ ያደርጋሉ? የሚያደርጉ ከሆነ መጠኑን ቢገልጹልኝ (በተደጋጋሚ ወይስ አልፎ አልፎ) የማያደርጉ ከሆነ ምክኒያቱን ቢገልጹልኝ፡፡ ……………………………………………………

   …………………………………………………………………………………….
2. አሁን በምታስተምሩበት የመምህርና የተማሪ መጻህፍት ውሰጥ የሚገኙትን የአንብቦ መረዳት ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ስልጠና ወስደዋል? ወስደው ከሆነ ለምን ያህል ጊዜ? ከስልጠናው በቂ ግንዛቤ አግኝተዋል? ………………………

   ………………………………………………….
3. ያንብቦ መረዳት ተግባራትን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ያጋጠመዎትን  ችግር ቢገልጹልኝ? ……………………………………………………………………..

   ……………………………………………

# ማረጋገጫ

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ብልሃት አተገባበር ፍተሻ በተመረጡ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራን ተተኳሪነት በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርስ በሂማኒቲስ፣ቋንቋዎች ጥናት፣ጆርናሊዘምና ኮሚኒኬሽንኮጅ ፣የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያለተሰራ የራሴ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኳቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለው፡፡

ስም፡- ---------------------------------------

ፊርማ፡----------------------------------------

ቀን፡-------------------------------------------